# ክርስቲያናዊ የሕይወት ስነ-ምግባር

በዲያቆን ወንድወሰን በቀለ

አዲስ አበባ፣ 1995 ዓ.ም

© ዲያቆን ወንድወሰን ሶርሳ መንገሻ

1995 ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::

All Rights Reserved

አድራሻ:- ዲ-ወንድወሰን ሶርሳ

ፖ.ሣ.ቁ. 81167

ስ.ቁ. 57 03 60 / 57 53 70

E-mail:- Wondwosen2002@freemail.com

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

የሽፋን ፎቶ :- የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን

**የመጽሐፍ ስጦታ**

ለ ______________________

ከ ______________________

ቀን ____________________

«በዕውቀት ዓለም ከሁሉ የከበረ ስጦታ የመጽሐፍ ስጦታ ነው::»

## መታሰቢያነቱ

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ባመጣው ሞት ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡና በተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች ሣቢያ ለጐዳና ሕይወት ለተጋለጡ ሕፃናት ወንድሞቼና እኅቶቼ ይሁንልኝ::

## ምስጋና

ይህንን መጽሐፍ አዘጋጅቼ ከጨረስኩ በኋላ ረቂቁን በማንበብና ሃሳቡን በማቅናት ለረዱኝ ለቀሲስ ከፍያለው መራሒ፣ ለመንፈሳውያን ወንድሞቼና እኅቶቼ፣ በሃሳብና በቁሳቁስ አቅርቦት ለመጽሐፉ ኅትመት ታላቅ አስተዋፅኦ ላደረገልኝ ለወንድሜ ለአቶ ታደለ ሶርሳ ከፍ ያለ ምስጋናዬን እያቀረብኩ እግዚ አብሔር በፍቅሩ ይባርካችሁ እላለሁ::

## ማውጫ


ገጽ

መቅድም

መግቢያ

ክፍል አንድ

*የመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት ደረጃዎች*

- *ሕፃን ማለት ምን ማለት ነው?* ................ 15
- *የሕፃናት ዕድገት* ................ 18
- አስተሳሰባችንን *ማመጣጠን* ................ 23
- *የመጀመሪያ* እንቅስቃሴ ................ 24
- *ለመሆኑ የሕፃንነት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ምን ይመስላሉ? የስሜት ሕዋሳቱስ ጠቀሜታ* እስከ ምን ድረስ ነው? ................ 27
- እንስሳትና አእዋፍ ................ 31
- ጨዋታ ................ 33
- ሳቅ ................ 40
- እንቅስቃሴ ................ 41
- ጩኸት ................ 43
- ጸሎት ................ 45
- ምናብ ................ 46
- እንቅስቃሴና ዜማ ................ 47
- ቸልተኝነትን ማስወገድ ................ 4[illegible]

- ኩረጃ ወይም ማስመሰል ........................ 49
- የፍቅር ኃይል .................................... 52
- ቅናት .................................................. 54
- የባለቤትነት ስሜት ............................. 55
- እውነታ .............................................. 56
- ቀለማት .............................................. 58
- ለውጥ የማፍቀር ባሕርይ........................ 59
- ሙገሳና ማበረታታት ............................ 61
- ማስፈራራት ......................................... 64
- ሕፃናትን የሚያሳስባቸው ጉዳይ ................ 66
- መስጠትና መስጠትን ማስተማር ........... 68
- የማስታወስ ችሎታ ............................. 69
- ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችና በዓላት ............. 72


## ክፍል ሁለት

### *ከፍተኛ የልጅነት ደረጃ*


- በመጀመሪያዎቹ የልጅነት ዓመታትና በከፍተኛ ልጅነት ደረጃ መካከል ያለው ልዩነት ...... 76
- ልዩነቶች ............................................ 78
- ማኅበረሰብ ......................................... 79
- ሰንበት ት/ቤቶች ................................. 80
- መንገር ................................................ 82
- ተገቢ ትምህርት .................................. 83
- ሕፃናት አማንያን ናቸው ...................... 86
- ታሪኮች ............................................. 89
- የስማዕታት ታሪኮችን የመተረኪያ ዘዴዎች... 91
- ቅጣት ................................................ 93
- የአካል ቅጣት .................................... 95
- የአካል ቅጣት የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ... 97
- ለአካል ቅጣት ምክንያት የሚሆኑ ሁኔታዎች.. 98
- የአካል ቅጣትና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ...... 101
- ለወላጆች ............................................ 105
- ዋቤ መጻሕፍት .................................... 110

# መቅድም

በዚህ መጽሐፍ ስለሕፃናት ሥነ-ልቦናዊና አካላዊ እንዲሁም አጠቃላይ ሰብዓዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ ለመረዳትና ከሕፃናት ጋር ያለንን ጤናማ ግንኙነት የተሟላና የተስተካከለ ለማድረግ የሚያስችሉንን ሃሳቦች በማንሳት ለመወያየት እንሞክራለን፡፡ በተጨማሪም ፍቅር፣ የዋህነትና ንጽሕና የተቀዳጀውን የሕፃናት ሰብዕና እንዴት ተንከባክበን መያዝ እንዳለብንና በመልካም አስተዳደግ እንዴት ልናንጻቸው እንደሚገባ እናያለን፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በአግባቡ ያልተኮተኮቱ ሕፃናት በራሳቸው፣ በቤተሰባቸውና በማኅበረሰቡ ላይ ምን ያህል አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ለመገንዘብ የሚያስችሉ ነጥቦችን እንዳስሳለን፡፡

በሰው ልጅ የዕድሜ እርከን ውስጥ የሰውን አጠቃላይ ህልውና፣ ሰብዕናና በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚኖረውን በጎም ሆነ አፍራሽ ሚና የሚወስኑ የተለያዩ የዕድሜ ደረጃዎች አሉ፡፡ ከነዚህ የዕድሜ ደረጃዎች መካከል ዋነኛውና የሰውን ልጅ ሕይወት የሚወስነው የልጅነት ጊዜ የሚባለው ወቅት ነው፡፡

ይህ የልጅነት ጊዜ ከልደት እስከ አሥራ አንድ ዓመት ያለውን የሚያካትት ሲሆን በማንኛውም ሕፃን የወደፊት ሕይወት ውስጥ ወሳኝ ሚና የሚጫወትና ጠንካራ

መሠረት የሚጣልበት ወቅት ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሕፃኑ የሚኖረው ባሕርይ ወይም በሕፃኑ አስተዳደግ ላይ የምናትመው አሻራ በሕፃኑ የነገ ሕይወት ላይ ወሳኝ ይሆናል።

በመሆኑም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ:-

ሀ. የቅድመ ልጅነት ጊዜ

ለ. የድህረ ልጅነት ጊዜ

የሚባሉትን የዕድሜ ደረጃዎች ባሕርያት በመዳሰስ ስለሕፃናት የሚኖረንን ግንዛቤ ለማዳበርና ለመልካም ሰብዕናቸው መታነፅ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ነጥቦችን በማንሳት ወላጆች፣ ቤተክርስቲያን፣ ማኅበረሰቡና ት/ቤቶች ከሕፃናት ጋር የሚኖረን ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበት የሚጠቁሙ ሀሳቦችን ለማንሳት እንሞክራለን።



## መግቢያ

ሕፃናት ገና ያልፈነዱ ልዩ ትኩረትና እንክብካቤ የሚያሻቸው እምቡጥ አበቦች፣ ለጋ ቀንበጦች ናቸው። እነዚህ ጮርቃ ቡቃያዎች ፍቅርን፣ ክብካቤን፣ አክብሮትንና ያላሰለሰ መንፈሳዊ ምግብን ይሻሉ። ሆኖም አብርካታ ጸሐፍት ትኩረታቸውን ዐዋቂዎች ላይ በማድረግ፣ ለአውደ ብዐዋቂዎች ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ጽሑፎችን ንባብ ሲያበቁ ማየት የተለመደ ክስተት ነው። ብዙዎችም ከነዚህ እምቡጥ አበቦች ጋር ከመጫወት፣ ከመወያየትና እነርሱን ለማስተማር ከመሞከር ይልቅ መላ ትኩረታቸውን በዐዋቂዎች ላይ ብቻ ያደርጋሉ። ባጭሩ ለሕፃናት በቂ ጊዜ ሰጥተው ሃሳብ ለመለዋወጥ ፍላጐቱና ፍቅሩ ያላቸው በጣም ጥቂቶች ናቸው።

ይህም በመሆኑ ሕፃናት ተገቢውን ትኩረትና አክብሮት የማይሰጣቸው መስሎ ስለሚሰማቸው በጩኸት፣ በረብሻ እና የግትርነት መንፈስ የተሞላባቸው ድርጊቶችን በማንፀባረቅ ተደማጭነትን ለማግኘት ይሞክራሉ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ሕፃናት አስተሳሰብ፣ እንዴት ልናጫውታቸው እንደሚገባና ፍቅራቸውንም እንዴት እንደምናገኝ እንዲሁም ማኅበራዊና መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እንዴት አድርገን ልናንፀው እንደምንችል በቂ ግንዛቤ እናገኛለን።

ልጆች ትልቅ ቦታ ሊሰጣቸው የሚገባ የቤተክርስቲያን ወይም የማኅበረሰቡ ዋነኛ አካል በመሆናቸው በአስተዳደጋቸው ሂደት በትክክል የምንረዳቸው ከሆነ አንድ መልካምና የኅብረተሰቡ አለኝታ የሚሆን ትውልድ አገኘን ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ የሕፃናትን ውሳጣዊ ማንነት ወይም ምንነት ሳንረዳ ቀርተን አቅጣጫ ከሳትን ድፍን ትውልድ በአንዴ አጣን ማለት ነው፡፡

ከሕፃናት እውነትን፣ ግልጽነትን፣ የዋህነትንና በጎነትን እንዲሁም ብዙውን ጊዜ በሀዋቂዎች ዘንድ የማናገኘውን ፈጣንና በጎ ምላሽ እናገኛለን፡፡ በመሆኑም ሕፃናትን ልንወዳቸውና ልናከብራቸው ይገባል፡፡ ከእነርሱም ጋር መጫወት፣ ማውራትና የቅርብ ጓደኛ እንዲሆኑ ማድረግ በጣም አስደሳች ሕይወትን ይፈጥራል፡፡

በመሆኑም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሃሳቦችና የሚነሱት ነጥቦች ሁሉ ከትምህርታዊ ምርምር ወይም ከጥልቅ የሥነ ልቦና ጥናት የተገኙ ብቻ ሳይሆኑ በአጸደ ሕፃናት፣ በሰንበት ት/ቤቶች እና በቤተሰብ ውስጥ ካካበቷቸው ልምዶች በመነሳት መምህራንና ወላጆች የሰጧቸውን አስተያየቶችንም ያካተተ ነው፡፡



# ክፍል አንድ

## የመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት ደረጃዎች

**ከልደት እስከ አፀደ ሕፃናት ያለውን የዕድሜ ክልል ይሸፍናል፡፡**

## ሕፃን ማለት ምን ማለት ነው?

ሕፃን ማለት እ.ኤ.አ ታህሣሥ 20 ቀን 1989 ዓ.ም ጸድቆ እ.ኤ.አ ከመስከረም 2 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ ባለው የሕፃናት መብቶች ስምምነት (Convention) መሠረት እንደ ሀገሩ ሕግ ከዚህ ባነሰ ዕድሜ ለአካለ መጠን ካልደረሰ በቀር ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው::

በዚህ ጽንሰ ሃሳብ መሠረት የዕድሜው ጣሪያ 18 ዓመት ሆኖ ከዚህ ባነሰ የዕድሜ ደረጃ አባል አገሮች እንደየራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ሕፃን የሚለውን የዕድሜ ክልል መወሰን ይችላሉ::

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩን በአገራችን ሕፃን የሚለውን የዕድሜ ገደብ ብዙዎቹ 3 ዓመት፣ 5 ዓመት፣ ከፍ ካለ 9 ዓመት ድረስ ነው የሚሉ አሉ::

ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትምህርት አንፃር ሕፃን የሚያሰኘውን የዕድሜ ገደብ የሚያሳይ ግልጽ ማስረጃ በዚህ ጥናት ባናገኝም አንድ ሕፃን አዋቂ ሰው የሚሠራውን ማከናወን አለበት ተብሎ የሚገመትበት ዕድሜ 7 ዓመት ነው:: ይህ ዕድሜ በ40 እና በ80 ቀኑ ተጠምቆ ከሥላሴ የጸጋ ልጅነትን ያገኘ ማንኛውም ሰው ጾም የሚጀምርበት ዕድሜ ነው::

በአገራችን በተለምዶ የሕፃንነትን የዕድሜ ገደብ ለማስቀመጥ የሚሞከረው ለሕፃኑ ሊደረግለት በሚገባው ጥበቃ እንክብካቤ ላይ በማተኮር ሳይሆን ሕፃኑ ለቤተሰቡ



ሊያበረክተው በሚገባው አስተዋጽኦ ላይ ያመዘነ እንደሆነ ይስተዋላል::

ሌላው ቀርቶ ትምህርት ቤት እንኳን የሚላክበት ምክንያት ቢማር በተሻለ መልኩ ቤተሰቡን ይረዳ ይሆናል በሚል ግምት እንጂ ልጅ ትምህርት የመማር መብት እንዳለው በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚታወቅ ሆኖ አይደለም:: ሕፃናት የራሳቸው ሰብዕና፣ አመለካከት፣ እምነትና ፍላጐት ያላቸው መሆኑ ብዙውን ጊዜ ግንዛቤ ውስጥ አይገባም:: ስለሆነም ነው የቤተሰቡ ፍላጐት ብቻ ሊንፀባረቅ የሚታየው::

ይህ አመለካከት ደግሞ ሕፃናት በቤተሰብ ውስጥ የላቸውን ሚና የሚቀንስ ብቻ ሳይሆን፣ ፍላጐታቸው ሁሉ ከራሳቸው ሳይሆን ከቤተሰብ የሚመነጭ ስለሚሆን በሕፃናት አስተሳሰብ ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል:: ሕፃናት የሚያከናውኗቸው ሥራዎች ወይም ያሏቸው መብቶች ወላጆቻቸው በችሮታ የሚሰጥ እንጂ ራሳቸው ጠይቀው የሚያገኙት እንዳልሆነ ነው መገንዘብ የሚቻለው::

በአንድ ወቅት አንድ የካቶሊክ ጳጳስ «የዓለም ሕፃናትን ብትሰጡኝ መላዋን ዓለም ካቶሊክ አደርጋታለሁ::» ብለው ነበር:: እርግጥ ነው ጳጳሱ ይህን ያሉበት ዐቢይ ምክንያት ነበራቸው:: ሕፃናት አእምሮ አቸው ክፍትና የሰጡትን የሚቀበል ለማስተማር፣ ለማስ ልጠንና ለመግራት የማያስቸግሩ፤ መልካም ነገሮችን ሁሉ አግባብ ባለው መንገድ ከሰጠናቸው ውጤታማ ስለምንሆን

ነው:: ማንኛውም በሕፃናት ልቡና ውስጥ የምናትመው ነገር ሁሉ ወደፊት በሕፃናት የዐዋቂነት ዘመን ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል:: እንዲያውም የሥነ ልቡና ተመራማሪዎችና ጠቢባን የሰው ልጅ ጠባያት፣ ስሜቱ፣ ደካማና ጠንካራ ጎኑ ሁሉ የሕፃንነት ሕይወቱ ወይም የአስተዳደጉ ነፀብራቅ ናቸው በማለት ይናገራሉ:: በተጨማሪም እኒሁ የሥነ ልቡና ምሁራን የሰው ልጅ ጭንቀትና ሥጋት የምንለውና በውስጥ የሚዳብረው ገደብ የለሽ ውስጣዊ ውዥንብር አልያም ደግሞ በሰው ልጅ ባሕርይ ውስጥ የምናገኘው ድፍረቱ፣ ፈሪነቱ፣ በጥርጣሬ ወይም በማመንታት የተሞላ መሆኑ እንዲሁም ከሰዎች ጋር ባለው ማኅበራዊ ግንኙነት በራስ የመተማመን ስሜቱ ወይም ተጠራጣሪነቱ በአእምሮ ውስጥ ከተቀረፀው የልጅነት ሕይወት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ መሆኑን አበክረው ያስገነዝባሉ::

ከዚህ የምንረዳው የልጅነት ጊዜ በሰው ልጆች የወደፊት ሕይወት ላይ ጠንካራ መሠረት የሚጣልበት ወሳኝ ወቅት መሆኑን ነው:: ስለዚህ በመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት ለሚገኙ ሕፃናት ልዩ ትኩረት መስጠት እንዳለብን መገንዘብ ይኖርብናል:: እናም ይህ የልጅነት ጊዜ ሕፃናትን ለማስተማር፣ ለማሰልጠንና ለመግራት አመቺ ጊዜ ከሆነና የነገው ብቁና መልካም ሰብዕና የተጐናፀፈ ዜጋን ለማፍራት ምቹ ጊዜ ከሆነ ለምን የዓለም ሕፃናትን ወስደን አርቶዶክሳዊ አናደርጋቸውም::



## የሕፃናት ዕድገት

የሕፃን ዕድገት ማለት በጊዜ ሂደት ውስጥ በሕፃኑ ላይ የሚታይ አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ለውጥ ነው:: ዕድገት አቅጣጫ ያለው፣ መተንበይ የሚቻልና እስከተወሰነ ዕድሜ ድረስ ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው:: ለምሳሌ:- አንድ ሕፃን ሁኔታዎች ከተመቻቹለት የተስተካከለና የተሟላ ዕድገት ሊኖረው ይችላል:: የሰው ልጅ ከዘር ውርስ ያገኛቸውን ባሕርያት በተገቢው ምግብና ትምህርት እንዲታገዙ ከተደረጉለት እድገቱ ጤናማና የተፋጠነ ይሆናል::

የአካለ መጠን መጨመርና የእንቅስቃሴ መዳበር አካላዊ ዕድገት ሲባል፣ ምክንያት የማቅረብና የማገናዘብ ችሎታ መዳበር አእምሮአዊ ዕድገትን ይመለከታል:: ሥነ ልቡናዊ ዕድገት የግል ስሜት መዳበርን ሲያመለክት ማኅበራዊ ዕድገት ደግሞ በአእምሮ መብሰልንና የማኅበራዊ ግንኙነት ማዳበርን ያጠቃልላል:: የነዚህ ዕድገቶች ድምር ውጤት ደግሞ የሕፃኑን ሁለንተናዊ ማንነቱን (Personality) ይገልጻል::

ሰዎች በፍፁም አይመሳሰሉም:: በልምድ፣ በፍላጐት፣ በአመለካከት፣ በእምነት፣ በአካል ቅርፅ፣ በፍልስፍናና በመልክ ወዘተ ይለያያሉ:: ለምሳሌ የአካል ቅርፅ ልዩነት በሰብዕና ዕድገት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል:: የአካል ቅርፅ ልዩነት እያንዳንዱ ሰው ራሱን በተለየ መልክ እንዲያይ ያስገድደዋል:: ለምሳሌ:- ወፍራም፣ ቀጭን፣ ረጅም፣

አጭር፣ ቆንጆ፣ ፉንጋ... ወዘተ ሰው ስለራሱ አንድ አይነት አመለካከት እንዲያዳብር ያደርገዋል:: በተለይ ሕፃናት ሰዎች ስለነርሱ ባላቸው አመለካከት በእጅጉ ስለሚሳቡ እንዲህ ነህ እንዲያ ነህ ከማለት መቆጠብ ያስፈልጋል::

የአንድ ሕፃን ሰብዕና (Personality) ቅርጽ መያዝ የሚጀምረው በባሕርይው፣ በችሎታውና ከአካባቢው የተነሣ ነው:: ለዚህም ቤቱና ቤተሰቡ በጣም ጠቃሚ የሆነ አስተዋፅኦ አላቸው::

ከሕፃኑ በስተቀር ማንኛውም ነገር አካባቢ ይባላል:: አካባቢ ተፈጥሮአዊ /አገር/ ማኅበራዊ /ሰዎች/ና ባሕላዊ /ወግና ልማድ/ ተብሎ ይጠራል:: አካላዊና አእምሮአዊ ዕድገት ከዘር የተገኘ የውርስ ውጤቶች ሲሆኑ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ዕድገቶች ደግሞ የአካባቢ ውጤቶች ናቸው:: አካባቢ ካልተስተካከለ ዕድገት በተገቢ ሁኔታ አይከናወንም::

የአንድ ሕፃን የመጀመሪያ አካባቢው የእናቱ ማህፀን በመሆኑ የእርሷ ሁኔታ የተመቻቸ ካልሆነ የፅንሱ እድገት እንከን አያጣውም:: ሕፃኑ እንክብካቤን፣ ፍቅርንና የደኅንነት ስሜትን ልምድ የሚቀስመው ከእናቱ ነው:: በቤት ውስጥ ከእኅት ከወንድሞቹ፣ ከሚያድግበት አካባቢ፣ ከማኅበራዊ ተቋማት፣ ከቤተክርስቲያንና ከትምህርት ቤት ለሰብዕናው መዳበር የሚረዱትን ነገሮች ስለሚማር አካባቢው የተስተካከለ ሊሆንለት ይገባል::

ዕድገት በተለያየ አቅጣጫ ይከናወን እንጂ አንዱ



ዓይነት ዕድገት ከሌላው ጋር የተቆራኘ ነው:: አካላዊ ዕድገት በተፈለገው መንገድ እንዳያድግ መሰናከል ገጠመው ማለት /ለምሳሌ:- የምግብ እጥረት/ አእምሮአዊ ዕድገቱም ችግር ገጠመው ማለት ነው:: የተስተካከለ አእምሮ የሌለው ሰው ስሜቱን በሚገባ ለመግለጽ ባለመቻሉ /ሥነ ልቦናዊ/ ውስጠ ስሜታዊ ዕድገቱም ተጓጐለ ማለት ነው:: ስሜቱን መግለፅ ያልቻለ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብቶ ለመኖር ስለሚያዳግተው ማኅበራዊ ዕድገቱም ኋላ ቀር ይሆናል:: ስለዚህ የሰው ልጅ ዕድገት አንድነትም ልዩነትም ባለው መልክ ስለሚከናወን ለሕፃናት ዕድገት አስተዋፅኦ የማቅረቡ ሁኔታ በአንድ ነገር የተወሰነ አይደለም:: ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ ኅብረተሰብና መንግሥት ለሕፃኑ የተስተካከለ ሰብዕና ዕድገት ሊያበረክቱት የሚገባ የማይናቅ ድርሻ አላቸው:: ሰብዕናው ያልተስተካከለ ሰው ኃላፊነትን ለመሸከምና ግዴታውን በተገቢው መንገድ ለመወጣት ስለማይችል ኅብረተሰቡ ወደፊት አገርን ተረክቦ ወደ ብልፅግና የሚያራምድ ትውልድ ለማፍራት የግዴታ ሕፃናትን በእንክብካቤ መያዝና ማሳደግ ይጠበቅበታል::

ሰው ማኅበራዊ ሕይወትን የሚመራው በውስጣዊ ስሜቱ (emotions) መኖር የተነሣ ነው:: ሌላው ሲደሰት የምንደሰተው ሲከፋ የምንከፋው፣ ሲያዝን የምናዝነው... ወዘተ ከውስጣዊ ስሜት መኖር የተነሣ ነው:: ውስጣዊ ስሜት በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ጠቃሚ ድርሻ አለው::

የሰው እንቅስቃሴ የሚከናወነው ከውስጣዊ ስሜት የተነሣ ነው። ውስጣዊ ስሜት የሌለው ሰው የሞተ ብቻ ነው። በሰው ሕይወት ውስጥ ማፍቀር፣ መጥላት፣ መቆጣት፣ መፍራት ... ወዘተ ያለ ነው። ይህ ስሜት የሚጀምረው በጨቅላነት (Infancy) ዘመን ነው የሚሉ ሲኖሩ ከዚያ ቀደም ሲል መኖሩንም የሚያስረዱ አሉ።

ውስጣዊ ስሜት በመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዘመን በዘፈቀደ ይገለፃል። ከዚያም በትምህርት /ልምድ/ ይገራል። ዕድሜ እየጨመረ ሲሄድ የመገራቱ ሂደት የተሳካ እንዲሆን ማሰልጠንን ይጠይቃል። ያልሰለጠነ ውስጣዊ ስሜት ሰብዕና (Personality) ላይ ችግር ያስከትላል። ለምሳሌ:- ቁጣ ከመጠን በላይ በሆነ መንገድ ሲገለፅ ግለሰቡ ራሱን መቆጣጠር አይችልም። ይህም ቁርጠኛ በሆነ መንገድ ውሳኔ መስጠትን ያዛባል። ስለዚህ ሕፃናት መልክ ባለው ሁኔታ ውስጣዊ ስሜታቸውን እንዲገልጹ ለማስቻል በትምህርታቸው መታገዝ አለባቸው።

ሰው ሕይወቱን በግልና በጋራ ይመራል። በመሆኑም ትብብር ያሳያል። ለዚህ ድርጊቱ ደግሞ ማኀበራዊ ዕድገቱ ሊዳብር ይገባዋል። አንድ ሰው በዕድሜው መጠን ማድረግ የሚገባውን የማያደርግ ከሆነ ማኀበራዊ ዕድገቱ አልዳበረም ማለት ነው። አንድ ሕፃን እያደገ በሄደ ቁጥር ከኅብረተሰቡ ጋር ያለው ግንኙነት እየሰፋ ይመጣል። ከተረጅነት ደረጃ ኅብረተሰቡን ወደ ማገልገልና መምራት



ደረጃም ይሸጋገራል። ይህም የሚሆነው ማኀበራዊ ብስለቱ ከፍተኛ ከሆነ ነው። ከዚህ በተቃራኒው የቆመ ከሆነ ደግሞ ባሕርይው የተገራ ስለማይሆን ፀረ ኅብረስተብ አቋም ይይዛል። የበታችነት ስሜት ስለሚሰማው ለኅብረሰተቡ በጐ ነገር ማድረግ ይሳነዋል።

የፆታ ልዩነት፣ የባሕል ተፅዕኖ፣ የኢኮኖሚ ይዞታና የቋንቋ መዳበር በማኀበራዊ ዕድገት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። ነፃ በሆነ ባሕል ውስጥ ያደገ ሕፃን ነፃ የሆነ አስተሳሰብ የማዳበሩን ያህል በጠባብና ቁጥጥር በበዛበት ባሕል ውስጥ ያደገ ሕፃን አስተሳሰቡና አመለካከቱ ጠባብ ነው። በዝቅተኛ ኑሮ ከሚመራ ቤተሰብ የወጣ ሕፃን የበታችነት ስሜት እንዲያድርበት የሚያደርግ ሁኔታ ከተፈጠረ በማኀበራዊ ሕይወት ውስጥ በሚደረገው ውድድር ላይ ወደኋላ ይቀራል። ከተቃራኒው ቤተሰብ የወጣ ደግሞ በራስ የመተማመን ባሕርይ ያሳያል። ሰው ሃሳቡን የሚገልፀው በቋንቋው በመሆኑ ቋንቋው እየዳበረ ሲሄድ ሌሎችን በረጋ፣ በታቀበ፣ በቀላልና በቀና መንገድ ያናግራል።

የትምህርት ዓላማ የሰውን ያልተገራ ባሕርይ ማሰልጠንና ሥርዓት ማስያዝ ነው። በተጨማሪም ሕፃኑ ኅብረተሰቡ የሚፈልገው ዓይነት የተስተካከለ ጠባይ እንዲኖረው ማስቻል ነው፡ ሰላምና ደስታ፣ የተገራ ባሕርይ እንዲኖር ማድረግና ተግባብቶ መኖር የሚገኘው በትምህርት ነው። አገልግሎት መስጠትን፣

መሥዋዕትነትን፣ ፍቅርን፣ መተባበርን፣ ርኅራኄን፣ ደግነትን፣ መግባባትን፣ ነፃነትን፣ እኩልነትን ... ወዘተ በቤት ውስጥ ቢማርም እንኳ መሠረት የሚይዘውና የሚጠናከረው በትምህርት ቤት ነው:: ስለዚህ በትምህርት ቤትና በወላጅ መካከል የጠነከረ ግንኙነት መፍጠር ተገቢ ይሆናል::

## አስተሳሰባችንን ማመጣጠን

የመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት የራሱ የሆኑ ልዩ ባሕርያት አሉት:: ይህ ጊዜ ሕፃናት ከሌሎች የዕድሜ እኩዮቻቸው ጋር በመቀላቀል አእምሮአቸውን የሚያዳብሩበት ጊዜ ነው:: በመሆኑም ይህ ወቅት ሕፃናት በመጫወቻ ቦታዎች፣ በማሳደጊያና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ለመቆየት ተስማሚ ሁኔታዎች የሚያመቻቹበት ጊዜ ነው:: በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናትን ባሕርይ ጠንቅቆ መረዳት ከሕፃኑ ጋር ለሚኖረን መልካም ግንኙነት ወሳኝነት ይኖረዋል:: በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሕፃኑ ተስማሚና ደረጃውን የሚመጥኑ ሃሳቦችንና ጨዋታዎችን ማካፈል አስፈላጊ ነው::

ምንጊዜም ቢሆን በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት ማድረግ የሚገባን ተቀዳሚ ተግባር እንደ ሕፃናቱ የአስተሳሰብ ደረጃ ዝቅ ብለን በመውረድ ማውራት መቻል ነው:: በፍፁም ከሕፃናቱ አስተሳሰብ በላይ በሆነ መንገድ ሕፃናትን ማነጋገር የለብንም:: በመሆኑም የሕፃናቱን ውስጣዊ ስብዕና በመረዳት ምን እንደሚወዱና ምን



እንደሚጠሉ ጠንቅቆ በማወቅ ከፍላጐታቸው ጋር ተጣጥሞ ለመዝለቅ መሞከር እንዲሁም ሁልጊዜ እንደ ጓደኛቸውና ረዳታቸው አድርገው እንዲቆጥሩን ይህንን በጎ ስሜት ማሳደር መቻል ለግንኙነታችን እንደ ማዕዘን ድንጋይ የሚቆጠሩ ዐበይት ነገሮች ናቸው::

ከዚህ ነጥብ ጋር የሚሄድና ሁኔታውን ቁልጭ አድርጐ የሚያመለክት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ1ቆሮ. 9÷20 እና 22 ላይ የተናገረው ነው:: «. . . ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ፣ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ::» ስለዚህ ከሕፃናት ጋር ሕፃን በመሆን ልናወራ ልንጨዋወትና ሃሳብ ልንለዋወጥ የሚገባ ሲሆን በተቃራኒው ይህንን ማድረግ የተሳነን ከሆነ ሕፃናቱን መረዳት ባለመቻላችን ውጤቱ መልካም እንደማይሆን ማወቅ ይኖርብናል::

## የመጀመሪያ እንቅስቃሴ

ለምሳሌ አንድ ቤተሰብ ለመጎብኘት ሄድን እንበል:: በጉብኝታችን የመጀመሪያ ቅፅበት ውስጥ ሕፃናት እንዳጋጠሙን ሕፃናቱን ለማቀፍ ወይም ከሕፃናቱ ጋር ለመቀለድ ከቶውንም መጣደፍ እንደሌለብን ልንረዳ ይገባል:: ምናልባት ይህን በማድረጋችን ሕፃናቱ የተቃውሞና የቁጣ ስሜት በማሳየት ሊርቁን ይችላሉ:: እኛ ደግሞ ልንጠላቸው አልያም ደግሞ ከሕፃናቱ ጋር

ልንፈጥረው የነበረውን ግንኙነት እንድንተው ልንገደድ እንችል ይሆናል::

ስለዚህ ከሕፃናት ባሕርያት ልናውቀው የሚገባው ዋናውና ተቀዳሚው ቁም ነገር ሕፃናት መጀመሪያ ገና አዲስ ሰው ሲያዩ ሰውየውን በአትኩሮት በመመልከት የሚመረምሩና ከሰውየው ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን ግንኙነት ለመወሰን በጥልቀት የሚያጤኑ መሆናቸውን ነው:: በመሆኑም ሕፃናቱ ቶሎ ለመቅረብና ለመጫወት ባይደፍሩ ሊደንቅ አይገባም:: እንዲያውም ሕፃናቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጋፊነት ባሕርይ ቢያሳዩንም እንኳ ይቅርታ ልናደርግላቸው ይገባል እንጂ ከቶውንም ጥላቻን በጥላቻ ልንመልስ አይገባም:: ሕፃናቱ ለተወሰነ ጊዜ ይህን ባሕርይ የሚያሳዩበት ዋነኛ ምክንያት ከአዲስ ሰው ጋር አዲስ ግንኙነት ለመመሥረትና ወደ አዲስ የሕይወት መስተጋብር ውስጥ ለመግባት በሚያደርጉት መፍጨርጨር አዲስ ዓለም ውስጥ የመግባት ያህል ስለሚሆንባቸው ነው::

ሕፃናት ገና ከጅምሩ አንድ አዲስ ሰው ሲመለከቱ ከሰውየው አጠቃላይ አካላዊና መንፈሳዊ ገፅታዎች ላይ አስተማማኝ የሆነና እርግጠኛ ሊሆኑበት የሚያስችላቸውን የደኅንነት ዋስትና ማግኘት ይሻሉ:: በሰውየው መልክ፣ ድምፅ እንዲሁም እንቅስቃሴዎች ሊሳቡ ከቻሉ በራሳቸው በመተማመን ያን ሰው በቀላሉ ይቀርቡታል::

<u>ለምሳሌ</u> ሽብርና ፍርሃት ሊፈጥሩባቸው ከሚችሉ



ነገሮች መካከል አንዳንዶቹን እንመልከት:: ከዚህ በፊት ሕፃናቱ ፊቱን ሪዝ የወረረው ወይም ጥቅጥቅ ያለ ጢም ያለው ሰው አይተው የማያውቁ ከሆነ ወይም ደግሞ ትልልቅና የደፈረሱ ዓይኖች ይዞ ሌሎች ሕፃናትን ሲቆጣ፣ ጆሮአችሁን እቆርጣለሁ እያለ ሲያስፈራራ አይተው ከሆነ ሕፃናቱ መሰል ሰው ሲመጣባቸው ሊፈሩና ሊሸሹ ይችላሉ::

እንግዲህ ሕፃናትን የፊት ገፅታችን ሁኔታም ሊያስፈራቸው እንደሚችል ከተረዳን ሕፃናት ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ ስንገባ ከላይ የተገለፀውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሳቅና ፈገግታ የተሞላበት መስህብነት ያለው ገፅታ በማሳየት ረጋ ብለን ለመቅረብ በመሞከርና ስሜታቸውን በመጠበቅ መልካም ግንኙነት መፍጠር እንችላለን:: ሌላው ቀርቶ ጠንከር ያለ ቃል ለሕፃናቱ ማስተላለፍ የግድ ሆኖ ቢገኝ እንኳ ያለምንም የፊት ማኮሳተርና ማጨማደድ የቃሉን ድምፀት ብቻ ጠንከር በማድረግ ልንነግራቸው ወይም የተፈለገውን መልእክት ልናስተላልፍላቸው ይገባል:: ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ ሕፃናቱ የቃሉን ትርጉም ሳይሆን በፊታችን ላይ የሚነበበውን ስሜት ነው የሚረዱት::

ለምሳሌ:- አንዲት እናት ልጇን በጣም ስትቆጣ ሕፃኑ የሚያስተውለው የእናቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ወይም ድርጊት በማየት የሚገነዘበውና በልቡ ውስጥ ዘልቆ የሚገባው ከእናቱ እንደበት የሚፈልቀት የቁጣ ቃላት

ሳይሆኑ በፊቷ ላይ የሚንተገተገው የቁጣና የንዴት ገፅታን ነው። ይህ የሚያየው ገፅታ ሕፃኑ እንዲፈራ እንዲሸበርና የሌሎችን እርዳታ ለማግኘት የድረሱልኝ ጩኸቱ እንዲያሰማ ያስገድደዋል።

ስለዚህ ቅዱስ ቃሉ «ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተው አትከልክሉአቸው» /ማር. 10÷14/ እንዲል ሕፃናትን ወደኛ ስናቀርባቸው ፈገግታን የተላበስንና ሩኅሩኅ ልብ ያለን ሆነን በመገኘት ልናቀርባቸውና ልንቀርባቸው እንዲሁም በፊታቸው ፍቅር፣ ሞገስና መስህብነትን የተላበስን ሆነን ልንገኝ ይገባል። እንግዲያውስ ከነዚህ ንጹሕ ቅዱስና ማራኪ ከሆኑ እምቦቃቅላዎች ጋር ያለንን ግንኙት ደስተኛ፣ ሰላማዊ፣ የተረጋጋና ከቁጣ የነፃ መልካም ግንኙነት በመፍጠር ወዳጅነታችንን አሐዱ ብለን ለምን አንጀምርም?

## <u>ለመሆኑ የሕፃንነት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ምን ይመስላሉ? የስሜት ሕዋሳቱስ ጠቀሜታ እስከ ምን ድረስ ነው?</u>

የመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት /Early Childhood or kindergarten/ የሚባለው የዕድሜ ክልል ከአገር አገር እንዲሁም ከሕፃናቱ የብስለት ደረጃ አንፃርና ከተጨባጭ ሁኔታዎች መለኪያ አኳያ በዚህ ያህል የዕድሜ ክልል ውስጥ ይካተታል ብሎ መናገር ባይቻልም ብዙዎች ግን ይህ የዕድሜ ክልል ከሦስት ዓመት እስከ ስድስት ዓመት ያለውን ጊዜ እንደሚሸፍን ይናገራሉ። ይህ ጊዜ ሕፃናቱ



ከሌሎች እኩያ ሕፃናት ጋር በመቀላቀል የማኅበራዊ ሕይወትና የስሜት ቃና በመፍጠር የሚያድጉበት ጊዜ ነው። በመሆኑም ይህ ወቅት በመጫወቻ ቦታዎች፣ በማሳደጊያና በአፀደ ሕፃናት አካባቢ ለመቆየት የሚያስችላቸው ጥሩና ምቹ ጊዜ ነው።

በዚህ የሕፃንነት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ሕፃናቱ ሊያሳዩአቸው የሚችሏቸው ባሕርያት የሚከተለውን ይመስላሉ። ይህ የዕድሜ ክልል በአብዛኛው ሕፃናቱ ጨዋታ የሚያበዙበት እንደመሆኑ አልፎ አልፎ ችኩ መሆን፣ የማጥፋትና የእምቢተኝነት ጠባዮችን በማሳየት የራሳቸውን መለያ ባሕርያት ለመመሥረት ፈር የሚቀዱበት ጊዜ ነው። እነዚህን ሁኔታዎች ጠቅለል አድርገን ስናያቸው ሕፃናቱ በመነጫነጭና ከሥርዓት ውጪ በመሆን ፍላጐታቸውን ሁሉ በረብሻ የሚገልጹበት ወቅት ነው። ለነዚህ ክስተቶች መንፀባረቅ ዋነኛው መንሥኤ ሕፃናቱ አካባቢውን ለመቆጣጠር ሲሉ ከውስጥ በሚፈጥሯቸው የስሜት ግፊትና በሕፃናቱ ዙሪያ ካለው ድባብ /Atmospher/ ጋር ለመጣጣምና ለመዋሐድ በሚያደርጉት ማኅበራዊ እንቅስቃሴ /Social Adjestment/ መካከል በሚፈጠር ግጭት የሚታይ የስሜት መገንፈል ነው።

እናም ይህ የዕድሜ ክልል ሕፃናቱ ለማኅበራዊ አኗኗራቸው መሠረት የሚጥሉበት፣ ሰዎችንና አካባቢን ለመረዳት ጉጉት የሚያድርባቸው፣ የተለያዩ ጥያቄዎችን

የሚያቀርቡበት እንዲሁም የሌሎች ሰዎችን እንቅስቃሴና ንግግር የመኰረጅ ሁኔታ የሚያሳዩበት ጊዜ ነው፡፡

እንግዲህ የመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት ባሕርያት ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ወቅት ሕፃናቱ ከአእምሮአቸው ይልቅ ስሜታዊ ግንዛቤዎችን የሚጠቀሙበት ጊዜ መሆኑን በአጽንኦት መጥቀስ ያሻል፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ሕፃናቱ አካባቢያቸውን የሚረዱትና የሚተረጉሙት በአእምሮአቸው ሳይሆን በስሜት ሕዋሳት መገለጫዎች ማለትም በሚያዩዋቸው፣ በሚሰሟቸው፣ በሚያጣጥሟቸው እና በመሳሰሉት ነው፡፡

በዚህ የዕድሜ ክልል ሕፃናቱ ከአእምሮአዊ ግንዛቤአቸው ይልቅ ስሜታዊ ግንዛቤአቸው ስለሚያይል ዝርዝር ታሪኮችና ገለፃ የበዛባቸው ተረቶችን ማጫወት በፍጹም አስፈላጊ አይሆንም፡፡ ከዚህ ይልቅ ሕፃናቱ ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች እጥርና ምጥን ባለ መንገድ እንዲሁም በቀላሉ ሊረዷቸው በሚችሏቸው ቃላት መልስ መስጠት የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት ከታሪኮች ይልቅ ሥዕሎችን ይበልጥ ስለሚወዱ በቪዲዮ ወይም በምስል የተደገፉ ትምህርቶችን መስጠት ይበልጥ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

ከላይ የተጻፈውን ሃሳብ የሚያጠናክር አንድ ገጠመኝ አለን፡፡ እ.ኤ.አ በ1963 ዓ.ም አንድ አባት ግብፅ ካይሮ ውስጥ በምትገኘው የአንባ ሬዌስ ( Anba Rewais) ቤተ



ክርስቲያን የአገልጋዮች ጉባዔ ላይ ንግግር እያደረጉ ሳለ አንድ ሕፃን በጉባዔው መካከል ሲገባ ያደረጉትን እንዲህ በማለት በጽሑፋቸው አሥፍረዋል፡፡ «ከልጁ ጋር ትንሽ የማውራትና ሃሳብ የመለዋወጥ ፍላጐት አደረብኝ እናም ምን ማውራት እንዳለብኝ አሰብኩ፡፡ በጊዜው በቤተ ክርስቲያኑ የሰንበት ት/ቤት ውስጥ ይሰጡ የነበሩትን ትምህርቶች ዝርዝር ተመልክቼ ስለነበር ሕፃኑን ስለተማረው ትምህርት ልጠይቀው ወደድኩ፡፡ እናም በሰንበት ት/ቤቱ ውስጥ ምን እንደተማረ ጠየኩት፡፡ ሕፃኑ ትንሽ ካሰበና ካመነታ በኋላ «የርግብ ትምህርት» የሚል መልስ ሰጠኝ ፡፡ በመልሱ በጣም ተገረምኩኝ፡፡ ምክንያቱም በሰንበት ት/ቤቱ ውስጥ ሲሰጡ የነበሩትን ትምህርቶች ዝርዝር ዐይቼ ስለነበርና በፕሮግራሙ ውስጥ ስለርግብ የሚያወራ ምንም ዓይነት ትምህርት ስላልነበረ ነበር የተገረምኩት፡፡

በዚህን ጊዜ የሰንበት ት/ቤቱ መምህርት ጣልቃ በመግባት በሰንበት ት/ቤቱ ውስጥ የተሰጠውን ትምህርት የሚያሳየው ሥዕል የትኛው እንደሆነ ጠየቀችው፡፡ በእርግጥ ሥዕሉ ጠርዝ ላይ በትንሹ የርግብ ሥዕል ትገኝ ነበር፡፡ ከዚህ ለመረዳት እንደሚቻለው የሕፃኑ አጠቃላይ ፍላጐትና ዝንባሌ የነበረውና ይበልጥ ስሜቱን የማረከው የትምህርቱ ይዘት ሳይሆን ርግብዋ እንደነበረች ነው፡፡ ይህም የሚያሳየን ሕፃናትን በቃል ብቻ ከምናስተምራቸው የበለጠ በሥዕል ብናሳያቸው ሊገባቸው እንደሚችል ነው፡፡

# እንስሳትና አእዋፍ

የመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት ከሚገለጡባቸው ወይም ከሚለዩባቸው ጠባያት መካከል አንዱ ሕፃናት ለእንስሳትና ለአእዋፍ ያላቸው ልዩ ፍቅር ይፋ የሚሆንበት ሲሆን በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ ሕፃናቱ እንስሳትንና አእዋፍን እንደተናጋሪ ፍጡሮች አድርገው ይቆጥሯቸዋል:: ሕይወት ያላትን ድመት ከልብ አቅፈው ሲያጫውቱ ወይም ደግሞ በድመትና በውሻ እና በሌሎች መሰል የቤት እንስሳት አምሳል የተሠሩ አሻንጉሊቶችን ሁሉ ሕይወት እንዳላቸው ፍጡሮች በመቁጠር ሲያዋሯቸው፣ ሲያቅፏቸው ሲያባብሏቸውና ሲያጫውቷቸው ማየት የዚህ ዕድሜ ክልል ባሕርይ መሆኑን እንገነዘባለን::

ይህ ወቅት ሕፃናት እንስሳትንና አእዋፍን ከልብ የሚወዱበት ጊዜ ነው:: በመሆኑም በአካል የሚዳሰሱ አሻንጉሊቶችን ብቻ ሳይሆን በሥዕላዊ መንገድ ተቀናብረው የቀረቡ ምስሎችን ሁሉ ሕፃናትን ለማጫወትና ለማዝናናት ብሎም ለማስተማር መጠቀም ውጤታማ ከሚያደርጉ መንገዶች መካከል አይነተኛው ነው::

__ለምሳሌ__:- የበልዓም አህያ /ዘኁ. 22÷1-ፍ.ም/ በድብ የተበሉት ሕፃናት /2ነገ 2÷23-25/ ወይም ሌሎችን ቀረቶችን በቃል /በተረት መልክ/ ከማስተማር ይልቅ በሥዕላዊ መንገድ ተቀናጅቶ በቀረበ ተከታታይ የሥዕል ትምህርት ሕፃናትን ብናስተምራቸው በእድሜያቸው መጠን የሚጠበቅባቸውን ዕውቀት ልናስይዛቸው እንችላለን::

በመሠረቱ በዚህ የሕፃንነት የዕድሜ ደረጃ የእንስሳትንና የአእዋፍን ታሪኮች . . . ወዘተ የሕፃናትን ምናብ /አእምሮአዊ የዕውቀት አድማስ/ የሚመጥንና ላሉበት ዕድሜ ተስማሚና አጥጋቢ በመሆኑ ከሥዕላዊ የማስተማሪያ መንገዶች በተጨማሪ በቪዲዮ ፊልም የተደገፉ ታሪኮችን ሕፃናት እንዲመለከቱ ማድረግ ጠቀሜታው ይበልጥ የጎላ ነው:: ከቴሌቪዥን ይልቅ በቪዲዮ ሕፃናትን ማስተማር ተመራጭ ነው:: ምክንያቱም የቲቪ ፕሮግራሞች ለሕፃናት ተገቢና መጣኝ የሆኑ ፕሮግራሞችን በማስተላለፍ ሂደት ልንተማመንባቸው ባለመቻላችንና በመተላለፊያ ሰዓቶች እርግጠኛ መሆን ባለመቻሉ ነው:: የቲቪ ፕሮግራሞች አጠቃላይ ከሕፃንነት እስከ ጉልማሳ ብሎም እስከ አዛውንት ዕድሜ ደረጃ ድረስ ያሉ ፕሮግራሞችን ሊይዙ ስለሚችሉ ሕፃናት የትኛውን መመልከት እንደሚኖርባቸው መምከር ቢቻልም የማይገባውን እንዳይመለከቱ ለመገደብ ግን አስቸጋሪ ነው:: በአንፃሩ የቪዲዮ ፊልም ጠቀሜታ የሚጐላው ለሕፃናት ተስማሚ የሚሆኑትን ፊልሞች በቀላሉ መርጦ አመቺ በሆነ ሰዓት ማሳየት ስለሚቻል ነው::

ስለዚህ ከላይ የተነሱትን ሃሳቦች መሠረት በማድረግ ነገሮችን በቀላሉና በፍጥነት ሊረዱ በሚችሉበት የዕድሜ እርከን ውስጥ የሚገኙትን ሕፃናት በሥዕላዊና በፊልም

በማስደገፍ በጎና ለወደፊት ሕይወታቸው መልካም ጥርጊያ መንገድ የሚከፍቱትን ትምህርቶች ለማስተማር መሞከሩ የዕለት ተዕለት ተግባራችን ሊሆን ይገባል።

## ጨዋታ

ጨዋታ በሕፃናት ሕይወት ውስጥ ልዩ ሥፍራ የሚሰጠው ታላቅ ቁምነገር ነው። ሕፃናትን ደስታና ሐሴት የሚያጐናፅፍ በመሆኑ ጨዋታን እጅግ አድርገው ያፈቅራሉ። ሕፃናት የሚወዱት ጨዋታን ብቻ ሳይሆን ለመጫወት የሚያስችሏቸውን ቁሳቁሶች የሚያበረክቱላቸውን ሰዎችም ጭምር ነው።

በመሆኑም ለሕፃናት ተስማሚና ጠቃሚ የሆኑ ጨዎታዎችን አመቻችተን ልናቀርብላቸው ይገባል። በመሠረቱ ለሕፃናት የጨዋታ ዓይነት መርጠን ከማጫወታችን በፊት አስቀድሞ ለራሳችን አቅርበን ምላሽ ልንሰጥባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች አሉ። እነርሱም ጨዋታውን ሕፃናቱ ይወዱታል? የምናቀርብላቸው የመጫወቻ ዕቃ ለሕፃናቱ ተስማሚና ለጉዳት የማያጋልጧቸው ናቸው? ትልቁና አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባው ደግሞ እኛ የምንፈልገውንና የምንወደውን ጨዋታ ሳይሆን ሕፃናቱ የሚወዱትን የጨዋታ አይነት ማቅረብ መቻላችን ነው።

በተጨማሪም ለሕፃናት መዝናናትና ደስታ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የጨዋታ አይነቶችን ብቻ ሳይሆን አእምሮአቸውን ሊያነቃቁ፣ የማንዛቤና የአስተሳሰብ



ደረጃቸውን ሊያጐለብቱ እንዲሁም ክሂሎቶቻቸውን ሊያዳብሩ የሚችሉ ጨዋታዎችን ማቅረብ ይጠበቅብናል። የዚህ አይነት ጠቀሜታ ካላቸው ብዙ ጨዋታዎች መካከል የተለያዩ ቀለም፣ መጠንና ቅርፅ ያላቸው የሸክላ፣ ፕላስቲክና ሌሎች መሰል ቁሶችን በማቅረብ የተለያዩ ዲዛይኖችን በመገጣጠምና በመበታተን እንዲገነቡ ማድረግ የሚያስችሉ ዘዴዎች ይገኙባቸዋል። እነዚህ ቁሶች ሕፃናት ትንንሽ ቤቶችን፣ ድልድዮችንና መንገዶችን እየገነቡ እንዲጫወቱ የሚያስችሉ ሲሆኑ ለአእምሮአቸው መዳበርና ለምናባቸው መስፋት ታላቅ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

እንዳንዴ ደግሞ ሕፃናት ከቤት እንስሳት ጋር አልያም ከጓደኞቻቸው ጋር መጫወትን በጣም ይወዳሉ። ሌላው እጅግ የሚያስደስታቸው ደግሞ በአፀደ ሕፃናት ውስጥ መጫወት ነው። በአፀደ ሕፃናት ውስጥ በሚገባ ታስቦባቸውና በጥናት የተዘጋጁ የተለያዩ ጨዋታዎችና ሕፃናትን እንደልባቸው እንዲሆኑና እንዲቦርቁ የሚያስችሏቸው ሰፋፊ ሥፍራዎች ወይም ሜዳዎች ከሚወዷቸው ነገሮች መካከል የሚመደቡ ናቸው።

በነዚህ ሥፍራዎች ብዙ ነገሮችን በመሞከር ይጫወታሉ። ለምሳሌ፦ ከአንዱ ከፍታ ወደ ሌላው መዝለል፣ ዛፍ ላይ ለመንጠልጠል መሞከር፣ ከእንጨት በተቀረፀ ፈረስ ላይ መጋለብ ፣ የመጫወቻ መኪናዎችን መንዳት ...ወዘተ የጨዋታ ስሜታቸውን የሚገልጹባቸው መንገዶች ናቸው።

እንግዲህ ከላይ የጠቀስናቸው ሕፃናት ከሚደሰቱባቸው የጨዋታ አይነቶች መካከል ናቸው:: ስለዚህ በመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት በሚባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት ተስማሚ፣ ምቹና የሚመጥኑ ጨዋታዎችን በማቅረብ ረገድ ጥንቃቄና ትኩረት ልናደርግ እንደሚገባ በአፅንኦት ለመግለፅ እንወዳለን::

ብዙዎች በቤታችን ላሉ ሕፃናት አስፈላጊና ተስማሚ የሆኑ ጨዋታዎች ለማቅረብ ባለመቻላችንና አመቺ ሁኔታዎችን ባለመፍጠራችን ሕፃናቱ በቤት ውስጥ በሚጫወቱባቸው አግባብ ባልሆኑ ቁሳቁሶች ሰቅጣጭ ድምፅ ሲፈጥሩ ወይም በዕቃዎች ላይ ጉዳት ሲያደርሱ ይስተዋላል:: እንዲያውም ብዙውን ጊዜ ሕፃናት ስህተት ሲሠሩና ሲያጠፉ ማየት የዕለት ተዕለት ገጠመኝ ሆኗል:: ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የወላጆች ቸልተኝነት ነው:: በተጨማሪም ወላጆች ለሕፃናቱ ጨዋታ ትኩረት ያለመስጠት ችግር በእጅጉ የሚያስወቅሳቸው ጉዳይ ነው::

እርግጥ ነው አንዳንድ ቤተሰቦች ለሕፃናት ልጆቻቸው ምቹ፣ ተስማሚና ልዩ የመጫወቻ ክፍል ሲያዘጋጁ ሌሎች በቤተ ክርስቲያን በሚገኙና በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ወይም በከተማው ጥሩ ስምና ዝና ባለው አፀደ ሕፃናት ልጆቻቸው እንዲገቡ ያደርጋሉ:: ይህ በራሱ ለሕፃናቱ ስሜትና አእምሮ መጎልበት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል:: ቢሆንም ሕፃናት ጊዜያቸውንና መላ ኃይላቸውን የሚጠቀሙበት የጨዋታ አይነት ማቅረብ ያለመቻል ችግር አለ:: በመሆኑም ከዚህ ጋር በተያያዘ ለአባቶች፣ ለእናቶች፣ ለአፀደ ሕፃናት እንዲሁም ሰንበት ት/ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ መምህራን የሚከተሉትን ወሳኝ ጥያቄዎች ለማንሳት ግድ ይለናል::

- ስለመሆኑ ሕፃናት እንዴት ነው ጊዜያቸውን ሊጠቀሙ የሚችሉት?
- በነዚህ ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ያቀረብንላቸው የጊዜ ማሳለፊያ ምንድነው?

ለቀረቡት ጥያቄዎች ወላጆችና መምህራን አጥጋቢ ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል:: በዚህ በምንወያይበት የመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት በሚባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት መልካም አስተዳደግ ብሩህ ተስፋ ይሆን ዘንድ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሚሰጠው ትክክለኛ ምላሽ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል:: ነገር ግን ምላሹ ልዩ ትኩረት ሳይሰጠው ከቀረ ክፉውንና በጎውን መለየት በማይችሉበት በዚህ የዕድሜ ደረጃ የሚገኙትን ሕፃናት ለጉዳትና ለጥፋት ማጋለጣችን አይቀሬ ነው::

በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት ለሕይወታቸው አደገኛ በሆኑ ነገሮች ሊጫወቱ፣ ሊጨብጡ እንዲሁም ወደ አፋቸው ሊከቱ ይችላሉ:: ለዚህ ነው በብዙ መድኃኒቶች ላይ **"ሕፃናት ከማይደርሱበት ቦታ ይቀመጥ"** የሚል ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ተጽፎ የሚገኘው:: በተጨማሪም የተለያዩና በቤት ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎችን አንስተው ሊወረውሩ፣ ጠቃሚ ወረቀቶችን ሊቀዱ፣ በጣም ውድና ተሰባሪ ዕቃዎችን

አንስተው ሊጫወቱባቸው አልያም ደግሞ በጠርሙስና በብልቃጥ ውስጥ የሚገኙ ፈሳሾችን ሊያፈሱ ይችላሉ::

በእነዚህና መሰል የሕፃናት ጥፋቶች ወላጆች በጣም ሊናደዱና ሕፃናቱን ሊቀጡ ይችላሉ:: እነዚህ ሕፃናት ያደረሱት ጥፋት ይሁን ልማት ለይተው መገንዘብ የማይችሉበት የዕድሜ ደረጃ ላይ ስለሚገኙ ለደረሰው ጥፋት በግንባር ቀደምነት ሊወቀሱ የሚገባቸው እነርሱ ሳይሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ያልቻሉት ወላጆቻቸው ናቸው::

በመሆኑም ወላጆችም ሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ዋጋ አላቸው ተብለው የሚታሰቡና በቀላሉ ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችሉ ዕቃዎችን ከሕፃናት ፊት በማራቅ ሕፃናቱን ካላስፈላጊ ጥፋትና ቅጣት ሊጠብቁ ያስፈልጋል:: ይህ ጥፋት ከሕፃናቱ ታዛዥ አለመሆን የመነጨ እንደሆነ አድርጎ መቁጠር ፈፅሞ ስህተት መሆኑን በአንክሮ ልንገነዘብ ይገባል:: ሕፃናት የምንነግራቸውን ሁሉ በትክክል እንዲፈፅሙና ትእዛዞችንም እንዲቀበሉ ተገቢ የሆነውንና የሚችሉትን ነገር እንዲያደርጉ መጠየቅ ይኖርብናል:: በፍፁም ከሕፃናት የተፈጥሮ ባሕርይ ጋር ሊጣጣም የማይችል ትእዛዝ ልንጭንባቸው አይገባም:: ታዛዥነታቸውም በነፃነታቸው ላይ የምንጥለው ገደብ መሆን የለበትም::



# ጨዋታ ለሕፃናት ያለው ጠቀሜታ

## ❖ መጫወት ማደግ ነው

የመጫወት ዕድል ማግኘት ለሕፃናት ጤናማ የአካልና የአእምሮ ዕድገት እንዲሁም ከሌሎች ከነርሱ ከሚበልጡ ልጆች ጋር ለመቀላቀል የሚኖራቸው ችሎታ እንዲዳብር ያደርጋል:: በመጫወት ሂደት ሕፃናት ከውጪው ዓለም ጋር ይተዋወቃሉ:: ምክንያቱም ጨዋታ የበለጠ ተጨባጭና በቀላሉ መማርንና ዕውቀት መቅሰምን ከፍ የሚያደርግ ዘዴ ነው::

## ❖ መጫወት መማር ነው

ከጤናና ከትምህርት አኳያ ጨዋታ ጠቀሜታ አለው:: ሕፃናት ጤናማ አካል ያስፈልጋቸዋል:: ጤናማ ከሆኑ ደግሞ የሚሰጠውን ትምህርት በቀላሉና በፍጥነት ሊቀበሉ ይችላሉ:: ጨዋታ ደግሞ የሰውነት ጤንነት በተገቢው መንገድ እንዲስተካከል ይረዳል:: በሽታን የመቋቋም አቅም እንዲኖር ከመርዳቱም በላይ በራስ መተማመንና አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎችን ለመቋቋም ያስችላቸዋል:: አካላዊ አቋማቸውንም ብቁ ያደርጋል::

- ጨዋታ ሕፃናት የሚማሩባቸውና ማንነታቸውን የሚፈትሹበት፣ ፍላጎታቸውን የሚለዩበትና የፈጠራ ሰው እንዲሆኑ የሚያግዝ ጠቃሚ ስልት ነው::
- ጨዋታ ሕፃናት ንቁ እንዲሆኑ ጡንቻቸው እንዲጠነክር ይረዳል::

- በተፈጥሮ ያላቸውን ግምት በመጠቀም በፍላጉታቸው በመመራት አካባቢያቸውን እንዲዳስሱ፣ ማሰብን እንዲማሩ፣ ባላቸው ኃይል እንዲተማመኑ ይጠቅማቸዋል፡፡
- ከሌላው ጋር እንዲቀራረቡና ጓደኛ እንዲያፈሩ ይረዳል፡፡

## ❖ ጨዋታ ለት/ቤት መዘጋጃ ነው

ሕፃናትን ት/ቤት በማስገባት ብቻ ማስተማር የሚቻል አይደለም፡፡ ጨዋታ ራሱ ሕፃናቱ ለትምህርቱ እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋል፡፡ በቅድመ ትምህርቱ ት/ቤት ገብተው ከመጽሐፍ ከሚያገኙት ትምህርት ያላነሰ በጨዋታ ይማራሉ፡፡ ሕፃናት ሲጫወቱ ከመጽሐፍ ውስጥ ስለሚያነቡት እውነታ በራሳቸው ይማራሉ፡፡ በዚህም እጃቸውንና ጣታቸውን ለመጻፍ እንዴት እንደሚጠቀሙበት ይረዳሉ፡፡ በመሆኑም የጨዋታ ዕድል ማግኘት ለትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ለአሻንጉሊቶቻቸው ጥንቃቄ ማድረግ መማር ራሱ የኃላፊነት ስሜት እንዲያድርባቸው ስለሚያደርግ ለወደፊት በትምህርታቸው ጠንካራ እንዲሆኑ ያግዛል፡፡

## የጨዋታ ዓይነቶች

1. *<u>የግል ጨዋታ</u>*- ዕድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ለብቻቸው ከአሻንጉሊት ጋር የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡



2. *<u>የምልከታ ጨዋታ</u>*፡- ዕድሜያቸው ሁለት ዓመት የሆናቸው ሕፃናት በዕድሜ ከፍ ያሉ ሕፃናት ሲጫወቱ በማየት የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡
3. *ንጽጽራዊ ጨዋታ*፡- ከ2 እስከ 3 ዓመት ባለ ዕድሜ ያሉት ሕፃናት በትውውቃቸው ውስንነት የተነሣ ጐን ለጐን በየራሳቸው መጫወቻ የሚያደርጉት ጨዋታ ነው፡፡
4. *<u>ተዛማጅ ጨዋታ</u>*፡- በ4 ዓመት ዕድሜ ሕፃናት መካከል አንዳንድ ቁሳቁሶችን በመሥራት በጋራ የሚደረግ ጨዋታ ነው፡፡
5. *<u>የኅብረት ጨዋታ</u>*፡- ከ5 ዓመት ጀምሮ ሕፃናት በመተጋገዝ በኅብረት የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡

## ሳቅ

ስለሳቅ የተነገሩ አያሌ አባባሎች አሉ፡፡ «ሳቅና ወፍር»፣ «ሳቅና ዕድሜህን አርዝም» እንዲሁም «ሳቅ የደስታ ምንጭ ነው» ወዘተ ፡፡ በርግጥ አባባሉ እንደሚያመለክተው ሳቅ የደስታ ምንጭ ነው፡፡ የሰው ልጅ ለመሳቅ አንዳች የደስታ ስሜት በውስጡ ሊፈጠር ይገባል፡፡ ከዚያ ደስታ ውስጥም ሳቃችን እንደ መስከረም አደይ ፈክቶ፣ እንደ ምንጭ ኩልል እያለ ይፈልቃል፡፡ ሕፃናትም የዋህና ንፁሕ የሆነው ተፈጥሮአቸው ሁሌም ደስታን የሚሻ በመሆኑ የሚያስቃቸውን ነገር ተግተው ይሻሉ፡፡

በዕለት ተዕለት ገጠመኝ ውስጥ ሕፃናት ያለ ምክንያት ሲስቁ ልናገኛቸው እንችላለን። በእርግጥ በአንክሮ ብናጤን ለሕፃናቱ ሳቅ መንሥኤ የሆነ ከአስተሳሰባቸው ጋር የሚጣጣም አንዳች ምክንያት ማግኘታችን አይቀርም። ምናልባት ሕፃናቱ ሊስቁ የቻሉት ለእነርሱ አእምሮ እንግዳ የሆነ ወይም ያልተለመደ ክስተት አሊያም ደግሞ አንድ አይነት እንቅስቃሴ በማየታቸው አለበለዚያም የሚደጋገምና የሳቅ ስሜት የሚጭር ቃና ያለው ድምፅ በመስማታቸው ሊሆን ይችላል።

ያም ሆነ ይህ በሳቅ አማካኝነት ሕፃናት የውስጥ ስሜታቸውን ይገልጻሉ። በተጨማሪም ሕፃናት እንዲስቁና እንዲደሰቱ ሊያደርጋቸው ከሚችል ሰው ጋር መገናኘታቸው በራሱ ሳቅ ሊፈጥርባቸው ይችላል። መስህብነት ባለውና እንዲስቁ ሊያደርጋቸው በሚችል ሰው ፊት ሁሌም መደሰታቸው ተዘውትሮ የሚታይ እውነታ ነው።

## እንቅስቃሴ

መቅበጥበጥ፣ መቁነጥነጥ፣ ወዲህና ወዲያ መሯሯጥ በአጠቃላይ የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ማድረግ የሕፃናት የተፈጥሮ ባሕርይ ነው። ሕፃናት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ግፊት የሚሰጣቸው ውሳጣዊ ኃይል አላቸው። በምንም አይነት ሕፃናት ሳያወሩ ወይም ሳይንቀሳቀሱ እጃቸውን አጣምረው ፀጥ ብለው እንዲቀመጡ ልናደርጋቸው አንችልም።



በመሆኑም ለሕፃናት እንደ ልብ መንቀሳቀስና ወዲያ ወዲህ ማለት የሚያስችላቸው ምቹና ሰፊ ቦታ ካላዘጋጀንላቸው እኛን ሊረብሽና ሊያውክ በሚችል መልኩ መንቀሳቀሳቸው አይቀርም። በዚህ ድርጊታቸውም ልንቆጣቸው ወይም ልንቀጣቸው እንችላለን። ለዚህ ደግሞ ተወቃሽ ሕፃናት ሳይሆኑ እኛው ራሳችን ነን።

ሕፃናት በሰንበት ት/ቤት ውስጥ በእንቅስቃሴ የታገዙ መዝሙሮችን በሚያስተምሯቸው መምህራን በጣም ሊደሰቱ ይችላሉ። ለምሳሌ፦ መምህራን ጥያቄ ሲጠይቋቸው መልስ ለመስጠት በጥድፊያ እጃቸውን ሲያወጡና ሲያወርዱ ሲነሱና ሲቀመጡ ራሳቸውን በእንቅስቃሴ የሚያጠምዱ በመሆናቸው በመምህራኑ ሊደሰቱ ይችላሉ።

በተፈጥሮ በመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት የዕድሜ ደረጃ ውስጥ የሚገኙትና እንቅስቃሴ አፍቃሪ የሆኑት ሕፃናት ሕዝበ ክርስቲያን ለጸሎትና ለሥርዓተ አምልኮ በተሰበሰቡበት ቦታ ለሁለትና ለሦስት ሰዓታት ያለ እንቅስቃሴ በፍጹም ሊቆሙ ወይም አርፈው ሊቀመጡ አይችሉም።

ስለዚህ እንቅስቃሴ የሕፃናት የተፈጥሮ ባሕርይ እንዲሁም ያሉበት የዕድሜ ደረጃ የሚያስገድዳቸው እስከሆነ ድረስ ከዚህ ተፈጥሮአዊ ድርጊት በቁጣ፣ በማስፈራራትና በኃይል ገድበን አርፈው እንዲቀመጡ ልናደርጋቸው አይገባም፤ አንችልምም።

ከቶውንም ቢሆን ሕፃናት እንደ ዐዋቂ እንዲሆኑ

ልንጫናቸው አያስፈልግም:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ1ቆሮ. 13÷11 ላይ «ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር÷ እንደ ልጅም አስብ ነበር÷ እንደ ልጅም እቆጥር ነበር፤ ጉልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ::» ሲል የተናገረው ለዚህ ላነሣነው ነጥብ አጋዥ ነው:: በፍጹም ከሕፃናቱ ዕድሜ ጋር የማይጣጣም ተግባር እንዲፈፅሙ ልናስገድዳቸው እንደማይገባ፤ በምንም ዓይነት ከሕፃናቱ ዕድሜ ደረጃ በላይ ብስለትን መጠበቅ እንደማይኖርብን ማወቅ ያስፈልጋል::

## ጩኸት

በተፈጥሮ የሕፃናት አንደበት ገና ያልተገራ በመሆኑ ምንጊዜም ከፍተኛና የሚረብሽ ድምፅ ያወጣሉ:: ለሕፃናት ማንኛውንም ነገር ቀስ ብሎ መናገር እጅግ አስቸጋሪና የማይቻል ሲሆን ብዙውን ጊዜ ጩኸታቸው የሚረብሽ ሆኖ ስናገኘው እንቆጣቸዋለን::

በመሠረቱ በመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን ለመግለፅ ቃላት ስለሚያጥራቸው ሃሳባቸውን በጩኸትና በለቅሶ ለመግለጽ ይሞክራሉ:: ይህ ሁኔታ ብዙዎችን በተለይም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ ቅዳሴ ወቅት ጸሎት ሲደርስ አሊያም ትምህርተ ወንጌል ሲሰጥ የሚረብሽ ሆኖ እናገኘዋለን::

በመሆኑም በአንዳንድ እኅት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለዚህ ችግር መፍትሔ ይሆን ዘንድ እናቶች ሕፃናት ልጆቻቸውን ይዘው ሥርዓተ ቅዳሴውንና ስብከቱን በድምፅ ማጉያ እየሰሙ የሚያስቀድሱበት «የመስታወት ቤት/Glass Room/» የሚባል ለብቻው የተዘጋጀ ክፍል አለ:: ይህ ክፍል በተለምዶ «የጩኸት ቤት (Crying Room)» እየተባለም ይጠራል:: በዚህ ክፍል ውስጥ ልጆቻቸውን ይዘው የሚቆዩት እናቶች በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚደረገውን ሥርዓተ ቅዳሴውንና ትምህርተ ወንጌሉን ከቤቱ ጋር በተገጠመው የድምፅ ማስተላለፊያ መሣሪያ ያዳምጣሉ:: ቤቱም ሙሉ በሙሉ ከመሥታወት የተሠራ በመሆኑ እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ለመመልከት ይችላሉ:: እንዲሁም ይኸው ቤት ድምፅ ወደውጭ እንዳያወጣ ተደርጎ ስለተሠራ የሕፃናቱ ድምፅ፤ ለቅሶና ጩኸት ሥርዓተ ጸሎቱን አያውኩም::

ሌላው ይህንን ችግር ለማስወገድ ያለው መፍትሔ ደግሞ ሥርዓተ ቅዳሴ ሲከናወን ወይም ስብከት ሲሰበክ ሕፃናቱ በሌላ ተግባር እንዲጠመዱና ጊዜያቸውን በቁም ነገር እንዲያሳልፉ የሚያደረግ ስልት ነው:: ይኸውም ሕፃናቱን መንፈሳዊ ሥርዓቱ ከሚከናወንበት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ወስዶ ትምህርት እንዲሰጣቸው የተለያዩ ተረቶች እንዲነገሩቸው፤ መዝሙር እንዲዘምሩ በማድረግ ማቆየት ነው::

## ጸሎት

ጸሎት የአንድ ክርስቲያን የዕለት ተዕለት ተግባርና ወደ ፈጣሪ መቅረቢያ መንገድ እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዳችን ሕፃናት ልጆቻችንን ለእግዚአብሔር አምላካቸው ተንበርክከው በመስገድ እጆቻቸውን ወደ ፈጣሪ በመዘርጋት ዘወትር የልመናና የምስጋና ጸሎትን ተግተው እንዲያደርጉ ከሕፃንነት ዕድሜያቸው ጀምሮ ማስተማር ይጠበቅብናል።

ሕፃናቱ የምናስተምራቸውን ጸሎት በአእምሮአቸው እስኪቀርጹና ለብቻቸው ጸሎቱን በሚገባ ለማከናወን እስኪችሉ ድረስ አብረናቸው በመደጋገም ልንጸልይ ይገባል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃ. 11÷2 «ስትጸልዩ እንዲህ በሉ ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ . . . » በማለት ለኛ ለሀዋቂዎቹም ጭምር በሰጠን መመሪያ መሠረት ሕፃናቱ ጸሎቱን እንዲለምዱትና ዘወትር ማስታወስ እንዲችሉ ማድረግ ይኖርብናል። በተጨማሪም ይኸው የጸሎት መመሪያ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ1ቆሮ 14÷26 ላይ በጻፈው መልእክቱ ተብራርቶ ተቀምጦልናል። «. . . በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፥ ትምህርት አለው . . . »

በመሆኑም በቤተሰብ ውስጥ ሳናሰልስ አዘውትረን የምናደርገው የጸሎት ሥርዓት በሕፃናት አእምሮ ላይ አዎንታዊ ውጤት ይኖረዋል። በቤት ውስጥ ወላጆች አዘውትረው ጸሎት ሲያደርጉ ሕፃናት ቢመለከቱ አብነት



ይሆናቸዋል። በተጨማሪም የቅዱሳንን ሥዕል፣ የጌታችንን መስቀል እንዲሁም ጧፍ ወይም መብራት ያለው ተለይቶ የተዘጋጀ የጸሎት ቤት መኖሩ ሕፃናት ሁሌ ጸሎት እንዲያደርጉ የሚያበረታታቸውና እንዲተጉ የሚያደርጋቸው ነው። እንዲሁም በሚያድጉበትና በጉልምስና ሕይወታቸው ለችግሮቻችን መፍትሔ ፣ ለሕማማችን ፈውስና ለልመናችን መልስ ከፈጣሪያችን ከእግዚአብሔር ዘንድ በጸሎት በመማለድ ማግኘት እንደምንችል እንዲያውቁና እንዲማሩ ያደርጋቸዋል።

## ምናብ

ሕፃናት በራሳቸው የአስተሳሰብ ደረጃና የአእምሮ አቅም የሚፈርጅ ያልተገደበ ምናባዊ /አንድን ነገር በስሩት የማለም ችሎታ/ ኃይል አላቸው። ይህ ምናባዊ ኃይላቸው በእውን ያልተከሰቱ ድርጊቶችን ፈጥረው ለመጻፍና ብሎም በእርግጠኛነት በማመን ለመተረክ የሚያስችላቸው ነው። ሕፃናት በምናብ የፈጠሯቸውን ታሪኮች በሚያወሩልን ጊዜ በፍጹም ውሸታም ናችሁ በማለት ቀልባቸውን ልንገፍና ልናስደነግጣቸው አይገባም።

ሕፃናት በምናብ የፈጠሯቸውንና በዓይነ ልቦናቸው የሚያይዋቸውን ወርቃማ የደመቁ ውብ ትዕይንቶች በውብ ኮልታፋ አንደበት እውነት አስመስለው ሲተርኩልን እየዋሹ እንዳልሆነ ልንገነዘብ ይገባል። እንዲህ አይነቱን ታሪክ በሚተርኩልን ወቅት ታሪኩ እንዴት እንደሚጓዝና እንደሚጠናቀቅ ትረካውን አብረን ሆነን እስከ

መጨረሻው ልንከተል ይገባል:: ወይም ደግሞ በሕፃናቱ የትረካ ሂደት እየተከታተልነው እኛንም ጭምር የታሪኩ ተባባሪ ደራሲዎች አድርገው እንዲቆጥሩን የታሪኩን አቅጣጫ ቀደም ተከተል በትጎትና እያረምን እያስተካከልን አብረን መጓዝ አለብን::

ስለሕፃናት ምናባዊነት ወይም የምናብ አቅም ሲወሳ ለጉዳዩ ዐቢይ ምሳሌ የሚሆን ከዛሬ ሃምሳ ዓመታት በፊት ተከስቷል ተብሎ የሚነገርለት አንድ ታሪክ አለ:: በዘመኑ ሰውየው ይኖርበት በነበረው ቤት ውስጥ የኤሌክትሪክ መብራት ስላልነበረ ሰውየው በነጭ ጋዝ በምትሠራው ቀጭን ረጅም የኩራዝ ብርሃን እየታገዘ መጽሐፍ ያነብ ነበር:: ካጠገቡ እየጮኸ፣ እየለፈለፈ የሚጫወት ትንሽ ልጅ አብሮት ነበር:: ታዲያ የልጁ ጨዋታ አባትየውን እየረበሸ ሲያውከው «እንደዚህ የምትረብሸኝ ለምንድነው? አሁን አንስቼህ እዚህ ኩራዝ ውስጥ ብከትህስ? » ይለዋል:: ልጁም «እህ! በኩራዟ ክር ተንጠልጥዬ እወጣለሁ» አለ ይባላል:: እንግዲህ ይህ የሕፃኑ ምላሽ ምን ያህል ሕፃናት ምናባዊ ኃይል እንዳላቸው የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ መሆኑን ማንም አሌ የሚለው አይመስለንም::

## እንቅስቃሴና ዜማ

ሕፃናት በእጅ፣ በጭንቅላት ወይም በፊት ገፅታ እንቅስቃሴ (Facial Expression) የዜማውን ስንኝ በትክክል እንዲያዜሙና ትርጉሙንም እንዲያውቁ ከረዷቸው እነዚህን በዜማ የታጀቡ የእንቅስቃሴ ስልቶች በደንብ



ሊያስታውሱና ሊያከናውኗቸው ይችላሉ:: እነዚህ እንቅስቃሴዎች እጅግ አድርገው ደስታ የሚፈጥሩላቸው ከመሆኑም በላይ በውስጥ ታምቆ ያለውን ኃይል እንዲጠቀሙበት ያግዛል::

ሕፃናት መልክም ጣዕመ ዜማ ያላቸው ዝማሬያትን ይወዳሉ:: ስለዚህ አንዳንድ መምህራን በዝማሬ አማካኝነት ሕፃናቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ስሞችን ማስታወስ በሚችሉበት መንገድ ያስተምሯቸዋል:: በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንና ጥንታዊ የቤተክርስቲያን ቃላትን በሚገባ እንዲማሩና ማስታወስ እንዲችሉ በእንቅስቃሴና በዜማ በታጀቡ ዝማሬዎች ያስተምሯቸዋል:: ይህ ስልት የሕፃናት የማስታወስ ችሎታ እንዲጎለብትና እንዲዳብር የሚያስችል ጥሩ ዘዴ ነው::

## ቸልተኝነትን ማስወገድ

ሕፃናትን በማጫወትና በማስተማር ሂደት አንዳንድ ተረቶችንና ታሪኮችን መንገር ያለብን በምን አይነት መንገድ ነው? በመሠረቱ የሕፃናት ባሕርይ የማያስለችና አጥር ምጥን ያሉ አዳዲስ ነገሮችን በመሻት ላይ የተመሠረተ ነው:: በመሆኑም ለሕፃናት ረጅም ታሪክ ልንነግር ብንጀምር ታሪኩ ላይ ትኩረት መስጠት ስለሚሳናቸውና ሃሳባቸው ስለሚበታተን ወዲያውኑ ታሪካችንን መስማት አቋርጠው በሌላ ነገር ላይ በማተኮር ራሳቸውን ያጠምዳሉ:: ለዚህ ዐቢይ ምክንያቱ የሕፃናት የዕድሜ ደረጃና የአእምሮ አቅም አጭር መልእክት

ያላቸው ታሪኮችን መስማትና በቀላሉ የሚገነዘቧቸውን ነገሮች ብቻ መውደድ ነው::

ምናልባት ለሕፃናት ረጅም ታሪክ መንገር ግድ ከሆነብን በክፍል በክፍል በመከፋፈል እያንዳንዱን ታሪክ አንድ ራሱን የቻለ አጭር ታሪክ በማድረግ ማቅረብ አለብን:: አለበለዚያ ታሪካችን መርዘሙ ሕፃናቱ እንዲሰለቹ ያደርጋቸዋል:: ስለዚህ የረዘሙና ሊያሰለቹ የሚችሉ ታሪኮችን በአጭር ባጭሩ እየቆራረጡ ለሕፃናት እንዲስማሙ አድርጎ ማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል::

ሌላው ሕፃናት የሚወዱትና ቀልባቸውን የሚስበው ድግግሞሽ ያላቸው ቃላትና ሐረጋት ሲሆኑ እነዚህ ቃላትና ሐረጋት እንደ መዝሙር ግጥም ጣዕመ ዜማ ቤት እየመቱና እየደፉ ሲደጋገሙ ለመንፈሳቸውና ለልባቸው አንዳች ሐሴትን ያጎናፅፉቸዋል::

## ኩረጃ ወይም ማስመሰል

በመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት የሌሎች ሰዎችን ድርጊቶችና እንቅስቃሴዎች ወዲያውኑ ኩርጀው ማስመሰል መቻላቸው አይነተኛ ባሕርያቸው ነው::

በመሆኑም የቤተሰብ አባላትም ሆኑ የአፀደ ሕፃናት ወይም የሰንበት ት/ቤት መምህራን በዚህ ጉዳይ ላይ ጠንቃቃና ጥሩ አርአያ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: ምክንያቱም ክፉና በጎውን ሳይለዩ ወዲያውኑ ያዩትን ነገር ተቀብለው የመተግበር ዝንባሌ ስለሚኖራቸው ነው::



ወላጆች ወይም ማንኛውም የቤተሰብ አባል ሕፃናቱ አዲስና እንግዳ የሆነ ቃል ሲናገሩ ከሰሙ ወይም ብልግና የተሞላበት እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ከተመለከቱ ይህን ድርጊት በአካባቢ ከሚገኙ ሌሎች ሰዎች፣ ከጐረቤት ወይም ደግሞ ከቴሌቪዥን አይተው ያደረጉት መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል::

ስለዚህ ከወላጆችና ከመምህራን የሚጠበቀው ሕፃናት ያሉበትን አካባቢ በተቻለ አቅም በሕፃናቱ አእምሮ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ክፉ ልማዶች ነፃ ማድረግ ነው::

ይህን በተመለከተ ብዙ ጊዜ በሕፃናት ሕይወት ውስጥ የከፋ አደጋ ሆኖ የሚገኘው ባልና ሚስት በሕፃናት ፊት ሆነው የሚለዋወጧቸው የስድብ ቃላትና ጠብ ናቸው:: እነዚህ ሁኔታዎች ሕፃናት የሰሙትን ነገር እንዲያንፀባርቁ ምቹ ዕድል ይፈጥራሉ::

እንግዲህ ወላጆች ሕፃናቱን ምንም ነገር ሊረዱ አይችሉም በሚል የተሳሳተ ግንዛቤ በልጆቻቸው ፊት አንጉል ቃላትንና የማይገቡ ድርጊቶችን ሲፈፅሙ ይታያሉ:: እርግጥ ሕፃናቱ ባሉበት የዕድሜ ደረጃ የሚወረወሩትን ቃላት ምንነት ጠንቅቀው ላይረዱ ይችሉ ይሆናል:: ነገር ግን ከዕለት ወደ ዕለት ሕፃናቱ እያደጉ የቃላቱን ትርጉም ይበልጥ እየተገነዘቡ ሲመጡ ሁሉን ነገር ልቅም አድርገው ያውቃሉ:: ከዚህ ባሻገር መዘንጋት የማይኖርብን ዐቢይ ነገር ሕፃናት በድምፅ ከሚሰሟቸው

ቃላት ይልቅ በዓይን የሚመለከቷቸው ጥሩ ያልሆኑ የፊት ገጽታዎችና ሌሎች የጥላቻ እንቅስቃሴዎች ይበልጥ ወደ አእምሮአቸው ፈጥነው በመግባት ውስጣቸው የሚቀረጹ መሆናቸውን ነው::

ስለዚህ የሕፃናት አእምሮ እንደ ነጭ ወረቀት ወዲያውኑ የተሰጠውን ተቀብሎ የሚያትም በመሆኑ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ አበክረን ለመግለጽ እንወዳለን::

ሕፃናት አንድ ስሕተት ሲፈጽሙ ስናገኝ በኃይለ ቃልና በጩኸት ከመገሠጽና ከመቆጣት ይልቅ በተረጋጋና ጨዋነት በተመላበት መንገድ አግባብ እንዳልሆነ ማስረዳትና ከጥፋታቸው መመለስ ይኖርብናል:: አለበለዚያ የእኛን አግባብ ያልሆነ የቁጣና የተግሣፅ መንገድ በመኮረጅ ሌሎች ላይ ሊያንፀባርቁ እንደሚችሉ ልንረዳ ይገባል::

ለማጠቃለል ሕፃናቱ በዕድሜ እየጎለመሱ ወደ ሰፊው ማኅበራዊ ሕይወት ከመቀላቀላቸው አስቀድሞ በልቦናቸው ጠንካራ የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆችን ማስጨበጥ በቀጣይ ሕይወታቸው ለሚያዩዋቸው፣ ለሚሰሟቸውና ለሚገጥሟቸው ተቃራኒ ድርጊቶች ወይም ክፉ ልማዶች መቃወሚያና የበጎ ምግባር መጠበቂያ ይሆኑላቸዋልና ነው::

ስለሆነም ወላጆች፣ መምህራንና የሰንበት ት/ቤት አካላት ሁሉ ያለባቸውን ኃላፊነት በግባቡ ለመወጣት



መሞከራቸውና ሕፃናትን የመልካም ሥነ ምግባር /የጥሩ ጠባይ/ ባለቤት ማድረግ መቻላቸው ነገ ለሚፈጠረው መልካም ዜጋ ከወዲሁ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል ማለት ነው::

ይህን በተመለከተ ወላጆች ለየት ያለ ኃላፊነት አለባቸው:: ትዳር ማለት የባልና የሚስት ተራ ግንኙነት ማለት ብቻ አይደለም:: ትዳር ታላቅ ኃላፊነት ያለበትና የነገውን ኅብረተሰብ በመፍጠር ረገድ ጉልህ ሚና የሚጫወት ጥምረት ነው:: ስለዚህ ወላጆች ድርብ ኃላፊነት እንዳለባቸው በአፅንኦት ማስገንዘብ እንወዳለን:: ምክንያቱም ከላይ እንዳየነው በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት ማንኛውንም የሚያዩትንና የሚሰሙትን ድርጊት ወዲያው ተቀብለው ከማንፀባረቃቸው ባሻገር ምሥጢር የሚባል ነገር አያውቁም:: ያዩትንና የሰሙትን ነገር በሌሎች ሰዎች ፊት መናገራቸው አይቀርም:: ስለዚህ ወላጆች በልጆች አስተዳደግ ላይ ጥንቁቅና አርቆ አሳቢ መሆን ይጠበቅባቸዋል::

## የፍቅር ኃይል

ማናቸውንም ነገር ለመቆጣጠር የሚያስችል ብቸኛ ኃይል ቢኖር አንድ እና አንድ ነው:: እርሱም ፍቅር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:: «በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸው ጸናጽል ሆኜአለሁ:: ትንቢትም ቢኖረኝ፥ ምሥጢርንም ሁሉና ዕውቀትንም ሁሉ ባውቅ፥

ተራሮችን እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ . . .» /1ቆሮ 13፥1፣2/

ፍቅር ያለው ሁሉም አለው:: ሕፃናትን ካፈቀርናቸው ልንቆጣጠራቸው እንችላለን:: ምክንያቱም ሕፃናት የሚወዷቸውን ይወዳሉ:: የሚወዷቸውን ይከተላሉ:: ይታዘዙለታልም:: ፈቃዱንም ይፈፅማሉ:: በተቃራኒው ፍቅራቸውን የማይቀበላቸውን ደግሞ የሚጐዳቸውና አደጋ የሚያደርስባቸው መስሎ ስለሚሰማቸው በጣም ይጠሉታል::

መቼም ልጆች እያለን የባለዋሽንቱን ታሪክ በተረት መጽሐፍ ላይ ሳናነብ የቀረን ብንኖር በጣም ጥቂቶች ነን:: በስፋት የሚታወቀው የባለዋሽንቱ ታሪክ የሚከተለውን ይመስላል:: ባለዋሽንቱ ወደ አንዲት መንደር ይገባና ልዩና መሳጭ ጣዕመ ዜማ ያላትን ዋሽንቱን መንፋት ይጀምራል:: ሕፃናት የዋሽንቱን ድምፅ ሰምተው ይሰበሰባሉ:: ባለዋሽንቱንም ይከቡታል:: እሱም ከአንዱ ቦታ ወደሌላው እየተዘዋወረ ሲነፋ ሕፃናቱ ከኋላው እየተከተሉ በደስታ ሲያጅቡት እንደገና ሌሎች የሕፃናት ቡድኖች ተሰባስበው መጥተው ሲቀላቀሉና በደስታ ሲቦርቁ የተጻፈውን እናስተውላለን:: ከዚህ የምንረዳው ሕፃናት የሚያጫውታቸውንና ፍቅር የሚሰጣቸውን ምን ያህል እንደሚያፈቅሩና እንደሚወዱ ነው::

እንግዲህ ሕፃናት የሚያጫውታቸውንና ፍቅር የሚሰጣቸውን የሚወዱ ከሆነ ለምን ልንቀርባቸውና ፍቅር



ልንሰጣቸው አንሞክርም? ፍቅራቸውን ካገኘን በኋላ ማናቸውንም እነርሱ ሊያውቁ የሚገባቸውንና የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ ልናስተምራቸው እንችላለን::

ሕፃናት በፍቅር የምናስተምራቸውን ነገሮች ለመቀበል ዝግጁ ናቸው:: በተለይ ደግሞ ግጥምና በእንቅስቃሴ የታጀቡ መዝሙራትን በፍጥነት የመረዳትና የመቀበል አቅም አላቸው:: ስለዚህ ፍቅር ይህን የማድረግ አቅም እንዳለው ካወቅን ለምን በፍቅር ሳይሰለቹ እንዲማሩ አናደርግም?

## ቅናት

ምንም ጊዜም ቢሆን ከሕፃናት ጋር ባለን የቅርብ ግንኙነት ጥንቃቄ ልናደርግበት የሚገባውና በአግባቡ ልናስተናግደው የግድ የሚለን ዐቢይ ምክንያት የሕፃናት ቀናተኛነት ነው::

ሕፃናት ተሰባስበው በሚገኙበት ሁሉ ቅናት ሊከሰት እንደሚችል ከወዲሁ መገንዘብ ይገባናል:: ለምሳሌ:- በአካባቢያችን ከሚገኙት ሕፃናት ለአንደኛው የበለጠ ሙገሳና ፍቅር ሰጥተን ሌላኛውን ችላ ብንል ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል:: ይህ ችላ የተባለው ሕፃን የቅናት ስሜት ሊያድርበትና ቂም ሊይዝ ይችላል:: ፍቅርንና ሙገሳን በማጣቱም ውስጡ በጣም ይጐዳል:: በመሆኑም በዚያኛው ሕፃን ላይ ቂሙን ለመወጣት የበቀል በትር ሊሰነዝር እንደሚችል ማወቅ ያሻል::

እዚህ ላይ የዮሴፍ ወንድሞች ታሪክ መጥቀሱ ተገቢ ነው:: የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍ ባለመው ሕልምና አባቱ ከፍቅሩ የተነሣ ባሰፋለት በኅብረ ቀለማት ባሸበረቀና ባማረ ቀሚስ ምክንያት የቅናት እሳት ውስጣቸውን በልቷቸው ዮሴፍን ለባርነት አሳልፎ እስከ መሸጥ አድርሷቸዋል:: /ዘፍ. 37+3/ ከዚህ የምንረዳው የሕፃናት የቅናት ባሕርይ ምን ያህል ከዐዋቂዎች እንኳ የከፋና የመረረ እንደሆነ ነው::

ስለዚህ ከሕፃናት ጋር ባለን ግንኙነት አንዱን ሕፃን ከሌላው ማስበለጥ፣ አንዱን ይበልጥ አቅርቦ ሌላውን ማግለል በፍጹም አይኖርብንም:: በእኛ ምክንያት አንዳቸው ከሌላኛው እንዳይጣሉ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል:: በአንድ አይነት መጫወቻ እንዳይጣሉ ለሁለቱም ተመሣሣይና አቻ የሆነ መጫወቻ ልናቀርብላቸው ያስፈልጋል:: ሁሌም ፍትሐዊ መሆን ይጠበቅብናል::

## የባለቤትነት ስሜት

ሕፃናት በማንኛውም ነገር ላይ ሙሉ መብት ያላቸው ሆኖ ይሰማቸዋል:: የወላጆቻቸው፣ የእንግዶች ወይም የወንድሞቻቸው የሆኑት ንብረቶች በሙሉ ልክ የራሳቸው ንብረት መስሎ ነው የሚታያቸው:: የሌላ ሰው ንብረት ነው ብሎ ለመቀበል አእምሮአቸው በፍጹም እሺ አይልም:: እጃቸው ያስገቡትን የማንንም ሰው ንብረት ለመውሰድ ብንሞክር ተቃውሟቸውን በጩኸትና በለቅሶ ይገልፃሉ::



በመሆኑም ሕፃናቱ ይህንን በማድረጋቸው ልንወቅሳቸው፣ ልንቆጣቸውና ልንሰድባቸው ብሎም ሌባ ወይም ቀማኛ የሚሉትን ቃላት በፊታቸው ልንጠቀምም አይገባም:: እነዚህ ቃላት ሕፃናቱ ሊረዷቸው የማይችሏቸው ከመሆናቸውም በላይ እነዚህን ቃላት በሌሎች ሰዎች ላይ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ::

ለምሳሌ:- ሕፃናት የነርሱ ያልሆነውንና የማይገባቸውን ዕቃ የኔነው በማለት ይወስዳሉ:: በዚህ ጊዜ ልንቆጣቸው ወይም መጥፎ በሆነ መንገድ የስድብ ቃላትን በመጠቀም ልናስደነግጣቸው አይገባም:: አስቀድመን አስፈላጊ የሆኑ ሊያበላሿቸው ይችላሉ ብለን የምንፈራቸውን ዕቃዎች በተቻለ መጠን መደበቅ ያስፈልጋል:: እንዲሁም መድኃኒቶችንና መሰል አደገኛ የሆኑ ቁሶችን ሕፃናቱ በፍጹም ከማይደርሱባቸው አካባቢዎች ማስቀመጥ ተገቢ ነው:: ድንገት እንኳ እነዚህን ነገሮች ይዘው ብናገኛቸው በኃይል መቀማት ወይም መንጠቅ ሳይሆን፣ በርጋታ በሌላ ሃሳባቸውን ሊሰርቅ በሚችል ምትክ ዕቃ አታሎ መቀበልና መደበቅ ያሻል::

## እውነታ

ሕፃናት ማለት ወደዚህ ኅብረተሰብ የሚቀላቀሉ አዳዲስ እንግዶች ናቸው:: ኅብረተሰቡ እንዴት ሊንከባከባቸውና ሊያስተናግዳቸው እንደሚችል እንዲሁም ራሳቸውን ለማን አደራ እንደሚሰጡ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም::

ሕፃናት ሁሌም የሚታመኑባቸውና የሚመኩባቸው ነገሮች የሉም:: እኛ ከምንሰጣቸው እውነተኛ ፍቅርና ከምናቀርብላቸው የሕይወት ገፀ በረከት በስተቀር::

ስለዚህ በምንገባላቸው ቃልም ሆነ ስለ ተለያዩ ነገሮች በምንሰጣቸው ማንኛውም መረጃ ታማኝ ሆነን ስንገኝላቸው ሕፃናት በኛ ላይ የሚኖራቸው እምነት ከብረት የጠነከረ ይሆናል::

የተፈጥሮ እውነታዎች እንደሚያስገነዝቡን የሕፃናቱ ንጹሕ ተፈጥሮ ግልጽነትና ቀጥተኝነት የተዋሐደው ስለሆነ ምንጊዜም ውሸት በሚለው ቃል ላይ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል:: ምናልባት የዚህን ቃል ፅንሰ ሃሳብና ትርጉም ካወቁት እኛኑ ውሸታም ብለው በቀጥታ ለመናገር ግልጽነትና ድፍረት አላቸው:: ይህ ብቻም አይደለም ሕፃናትን አንዴ ከዋሸናቸው ወደፊት በምንናገረው በማናቸውም ነገር ላይ እኛን ከማመን መታቀብ ይጀምራሉ:: ይህ ደግሞ በንጹሕ አእምሮአቸው ውስጥ አለማመንንና ጥርጣሬ እንዲኖር መንገድ ከፈትንላቸው ማለት ይሆናል:: በተለያዩ ምክንያቶች ሕፃናቱን ማታለላችን ወይም ቃላችንን አለመፈጸማችን ነገሮችን ያለማወሳሰብ በቀላሉ የሚቀበለውን ንፁሕ ተፈጥሮ ልናሳጣቸው ብሎም መደናገርና ውዥንብር ውስጥ ልንከታቸው ከመቻላችን ባሻገር እነርሱንም ሳናውቀው ውሸትና ማጭበርበር እንዲማሩና የከፋ ጉዳት እንዲደርስባቸው እናደርጋለን::



ማንም ሰው ቢሆን እንደ ሕፃናት ተፈጥሮን እንዳለች የሚረዳና የሚወድ የለም:: የዛፎች ውበት፣ የአበቦች ኅብረ ቀለምና መዓዛ፣ የባሕር ፀጥተኛነትና ግዝፈት፣ የወፎች መልክና ዝማሬ፣ የዓሣዎች ያሸበረቀ ኅብረ ቀለማዊ ድምቀት ሕፃናቱ በቃላት ሊገልጿቸው ባይችሉም የውስጥ ልባቸውን ነክተው በውበት አርክተዋቸው ሐሴትንና ደስታን የሚያጎናጽፏቸው ናቸው:: ለዚህ ነው ሕፃናት በሚለብሷቸው ልብሶች ላይ ከላይ የተጠቀሱት የተፈጥሮ በርካታ ምስሎች ሲኖሩበት ከፍ ያለ ደስታ የሚኖራቸው:: ይህ ብቻ አይደለም ሕፃናት ሥዕሎችን መመልከታቸውና ለመሣል መሞከራቸውም የሚያስደስታቸው ሌላ ነገር ነው::

## ቀለማት

ሕፃናት እጅግ ከሚማርኩባቸውና ከሚስቧቸው ነገሮች መካከል ቀለማት ልዩ ሥፍራን ይይዛሉ:: ሕፃናት ዓሣዎችንና ቢራቢሮዎችን ላሸበረቀው ኅብረ ቀለማቸው ሲሉ አጥብቀው ይወዷቸዋል:: ስለሚለብሷቸው ልብሶች ብናስብ ልብሱ ስለተሠራበት ቁስ ወይም ስለጥራቱና ዋጋው እነሱን አይገዳቸውም:: ትልቁና ብቸኛው ዋጋ የሚሰጠው ነገር ቢኖር የጨርቁ በኅብረ ቀለማት ማሸብረቅ ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዘፍ. 37+3 አባታችን ያዕቀብ ልጁን ዮሴፍን ለማስደሰት በኅብረ ቀለማት የተንቆጠቆጠ ቀሚስ እንዳሠራለትና ይህም ሁኔታ

አባትየው ዮሴፍን ከሌሎች ልጆች ሁሉ አብልጦ ይወደው እንደነበር የሚያረጋግጥ መሆኑን እናያለን::

ሌላው ቀርቶ ለሕፃናት ከረሜላ ወይም ቹኩሌት ስናድላቸው ለነርሱ ልዩ ትኩረትና መስህብ የሚሆናቸው ውስጥ ያለው ከረሜላ ወይም ቼኮሌት ሳይሆን የተጠቀለለበት ያሸበረቀውና በቀለማት የተንቆጠቆጠው ወረቀት ነው:: በቼኮሌት ወይም በከረሜላው ጥራት ላይ ያላቸው ፍላጎት በኋላ ሲቀምሱት የሚመጣ ጥያቄ ነው:: በመሆኑም ምንጊዜም ይበልጥ ሕፃናትን የሚያሳስባቸው ወይም ቅድሚያ እንዲሰጡ የሚያደርጋቸው የቀለም ጉዳይ ነው::

## ለውጥ የማፍቀር ባሕርይ

በሕይወት ውስጥ ምንጊዜም ለውጥ የመሻት ዝንባሌ የሕፃናት ብቻ ሳይሆን የማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር የተፈጥሮ ባሕርይ ነው:: ማንኛውም ሰው በዕለት ተዕለት የሕይወት እንቅስቃሴው ውስጥ አንድ አይነትና ድግግሞሽ የበዛበት ነገር ሁሉ መሰልቸትን ሊፈጥርበትና በነገሩ ጥላቻ ሊያድርበት መቻሉ አይካድም:: በዚህ ረገድ ደግሞ ከዐዋቂዎች በበለጠ ሕፃናት ላይ ቶሎ የመሰላቸት ሁኔታ ጎልቶ ይታያል:: በአጭሩ ለውጥን ከማንም በበለጠ ያፈቅራሉ ማለት ነው::

ለምሳሌ:- ሁልጊዜ በአንድ አይነት አሻንጉሊት መጫወት አይወዱም፤ ያሰለቻቸዋልና:: አንድ አሻንጉሊት ብቻውን ደስታ ሊሰጣቸው ወይም ሊያረካቸው አይችልም:: የአሻንጉሊት ቅርፅ ወይም መልክ መቀየር ተንቀሳቃሽ መሆኑ ወዘተ... ደስታ ሊጨምርላቸው ይችላል:: እንዲያውም ብዙ ጊዜ እንቅስቃሴ አልባ የሆኑ አሻንጉሊቶች ሲያስደስቷቸው አይታዩም:: ከእንቅስቃሴ በተጨማሪ ድምፅ የሚያወጡ መጫወቻዎች ይበልጥ ያስደስቷቸዋል:: አሁንም ደግሞ በነዚሁ መጫዎቻዎች ለረጅም ጊዜ መጫወት ያሰለቻቸውና የትኩረት አቅጣጫቸውን ወደሌላ በማድረግ አዲስ ነገር ፍለጋ ደግሞ ይሄዳሉ::

ይህ ለውጥ ፈላጊነት አዲስ ነገር የመሻት፣ የዕውቀትና የግንዛቤ አድማሳቸውን ለማስፋት የሚያደርጉት ሙከራ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል:: ሕፃናቱ ይህን የሚያደርጉት በቅድሚያ በስሜታዊ ግንዛቤ ሲሆን በሂደት እየበሰሉ ሲሄዱ በአእምሮአዊ ዕውቀት እየተገነዘቡ መጠቀም ይጀምራሉ::

ከዚህ በመነሣት በሰንበት ት/ቤት ለሚገኙ ሕፃናት የስሜት አቅጣጫ አመልካች የሆኑ መንገዶችን አስፈላጊነት ለመጠቀም እንወዳለን:: ይህም አዶቪዢዋል /ቲቪና ቪዲዮ/ የሚጠቀሙ ተቋማት ወይም ድርጅቶች የሕፃናትን ቀልብ ይበልጥ የመሳብ አቅም ይኖራቸዋል:: በተለይም ቴሌቪዥን በሕፃናት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተፅዕኖ በተመለከተ የሚመጣውን ወቀሳ መዘንጋት እንደሌለብን ሁሉ ሕፃናትን ለመሳብ ቴሌቪዥን የሚያበረክተውን በጎ አስተዋፅኦ በፍጹም ቸል ልንል ግን አይገባም::

ስለዚህ ምንጊዜም ቢሆን ለሕፃናት በጎና መልካም አስተዋፅኦ ያላቸውን አማራጮች ሁሉ ከማድረግ ልንታቀብ አይገባም፡፡

## ሙገሳና ማበረታታት

በአፀደ ሕፃናት ውስጥም ሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት ሁሉ ሙገሳና አድናቆትን ወይም አበረታች ቃላትን በጥብቅ ይሻሉ፡፡ ይህ ለነርሱ ታላቅ የፍቅር መግለጫ ምልክት ነው፡፡

ከቶውንም ቢሆን « ልጄ እጅግ በጣም ስለራሱ ኩራት የሚሰማው ወይም ከንቱ እንዳይሆንብኝ በጣም እጨነቃለሁ፡፡ በመሆኑም ሁሌም ኃጢአተኛ ፍጡር መሆኑን እንዲናገርና ትሑት እንዲሆን ላስተምረው እጥራለሁ» ማለት አይኖርብንም፡፡

እነዚህ አባባሎች ወይም የሕይወት ፍልስፍናዎች ለሕፃናት ተስማሚ አይደሉም፡፡ ይልቅ ሕፃናት በሚያደርጓቸውና በሚፈፅሟቸው ጥሩ ድርጊቶች ሁሉ ትክክለኛነት እንዲሰማቸው ልናሞግሳቸውና ልናበረ ታታቸው ይገባል፡፡

እርግጥ ነው የአንድ ሰው የብስለት ዕድሜ ደረጃ የሚባለው ሰውየው ክፉውንና በጎውን በራሱ መለየት የሚችልበት ሁኔታ ላይ ሲገኝ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማንም ሰው ሊያውቀውና ሊገነዘበው የሚችለው የአእምሮ ኃይሉን ተጠቅሞ ከሕይወት ልምድና ከትምህርት ዕውቀት መቅሰም ሲችል ነው፡፡



ነገር ግን በሕፃንነት የዕድሜ ደረጃ ሕፃናት ክፉውንና በጎውን የሚገነዘቡት ከኛ በሚያገኙት የሙገሳና የማበረታቻ ቃላት ነው፡፡ ለሠሩት መልካም ሥራ ስናሞግሳቸው ልክ እንደሆኑና ጥሩ እንደሠሩ ይረዳሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ሌላውን ድርጊት ከመፈፀም እንዲታቀቡ ስንነግራቸው ስህተት መሆኑን ይረዳሉ፡፡

ስለዚህ በማሞገስ ጥሩ ሰብዕና የተላበሰ የመልካም ዜጋ መሠረት እንዲሆን የምንሻውን ሕፃን ልናገኝ እንችላለን፡፡ ሕፃናትን በማሞገሳችን ሁሌም ለመልካም ሥራና ለቅን ተግባር እንዲነሣሡ እናበረታታቸዋለን፤ ፍቅራችንንም እንገልጽላቸዋለን ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ያሀል እናት ልጇን «አባባ ሥነ ሥርዓት ያለው ልጅ ይወዳል፡፡» ብላ ብትነግረው፤ ሕፃኑ ወዲያውኑ « እማማ፣ እኔ ሥነ ሥርዓት አለኝ፡፡ ደግሞም እኔ ረባሽ አይደለሁም፡፡» ብሎ ሲመልስ እናገኘዋለን፡፡ እንዲሁም «እግዚአብሔር ታናሽ ወንድማቸውን የሚያፈቅሩና ከነርሱም ጋር በሰላም የሚጫወቱ ልጆችን ይወዳል፡፡» ብላ ብትነግረው፤ ወዲያውኑ «እማዬ፣ እኔኮ ትንሿ እኅቴን በጣም እወዳታለሁ፡፡ ከርሷ ጋር መጫወትም በጣም ደስ ይለኛል፡፡» ብሎ ያለ ጥርጥር ሲመልስ እንሰማለን፡፡ ምክንያቱም ሕፃናት መወደድ፣ መፈቀር፣ መወደስ፣ መደነቅንና መሞገስን ስለሚወዱ ነው፡፡ በመሆኑም ሙገሳ በሕፃናት ግብ ውስጥ የመልካም ተግባር ሃሳብ እንዲቀሰቀስ የሚያደርግና ግፊት የሚጨምር መሣሪያ መሆኑን

ለአፍታም ቢሆን ቸል ልንል አይገባም።

የሕፃናት ተፈጥሮ ሙገሳ ሊያሰጡ በሚችሉና ቅጣት ሊያስከትሉ በሚችሉ ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት ለመገንዘብ ንቁና ፈጣን በመሆኑ ምንጊዜም ለሕፃናት ሙገሳና ማበረታቻ ተገቢ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ስለዚህ ሁሌም ቢሆን ሕፃናት መልካም ነገሮችን ፈፅመው ስናገኝ ማበረታታት ይኖርብናል ማለት ነው።

በአንፃሩ ስህተት ፈፅመው ብናገኛቸውስ? ምንድነው ማድረግ የሚኖርብን? ሕፃናት አንድ ስህተት ፈፅመው ስናገኛቸው የስድብና የተግሣፅ ናዳ ልናወርድባቸው አይገባም። ይህንን ከፈፀምን ምናልባት በቀጥታ የስድባችንን /አግባብ ያልሆኑ/ ቃላት ለቅመው በመውሰድ ሌላ ቦታ ላይ ሊጠቀሙበትና ይህንን ክፉ ልምድ እያዳበሩ ሊሄዱ ይችላሉ። ስለዚህ ሕፃናት ጥፋት ፈፅመው ሲገኙ ለበጎ ተግባራቸው እንሰጠው የነበረውን ሙገሳ፣ አድናቆት፣ ምሥጋናና ማበረታቻ መከልከል፤ ይህንን ባደርግን ጊዜ በርግጥም ስህተት እንደፈፀሙ ተረድተው ራሳቸውን ለማረም መጣራቸው አይቀሬ ነው።

በመሆኑም ምንጊዜም ቢሆን ሕፃናት የሰሙትን ነገር ሌላ ቦታ በመውሰድ ሊጠቀሙ ስለሚችሉ የስድብ ቃላት ላይ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል። ከሕፃናት ጋር የምናደርገው ጤናማና የተሳካ ግንኙነት ዐዋቂዎች የሆንን ሁሉ በመልካም ሥነ ምግባር የታነፁ /የተለበጡ/ ቃላትን እንደምን መገልገል እንዳለብን የሚያስተምረን ሲሆን



ሕፃናቱም ከኛ ኩርጀው በመውሰድ ሌላ ቦታ ሊጠቀሙ የሚያስችላቸውን ክፉ የስድብ ቃላት ከመገልገል ሙሉ በሙሉ ነፃ ያደርገናል። በመሆኑም ይህ የወላጆች፣ የወዳጅ ዘመዶችና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሁሉ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል።

እናም ሕፃናት በስህተታቸው የተነሣ መጠላትን ስለማይሹ፣ ክብርንም እጅግ አጥብቀው ስለሚፈልጉ የሚያበረታታቸውን ሰው ፍቅርና ሙገሳ ማጣት የማይፈልጉ በመሆናቸው «ልጄ አየህ እንደርሱ'ኮ አይደለም፣ እንደዚህ አታድርግ ... ይሄ ትክክል አይደለም ...» በማለት በትኅትና ልናስተምራቸው ይገባል።

ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁንና የክርስትና ሃይማኖት ከስድብና ከቁጣ ቃላት የጸዳችና ነፃ ነች። እርግጥ ነው መቼም ክፉ ልማድ የበጎ ተቃራኒ ነውና በተበሳጨን ጊዜ የስድብ ጽንሰ ሃሳብ ያዘሉ ቃላት መከሰታቸው አይቀሬ ቢሆንም እነዚህንም ቢሆን አሉታዊ ትርጉማቸውን በመተው አወንታዊ ቃናና ዘዬ እንዲኖራቸው አድርጎ በመጠቀም ሕፃናትን በጥሩ የሥነ ምግባር ባሕርያት፣ በቀና መንገድ ተኰትኩተው እንዲያድጉ ልናስተምራቸው እንችላለን።

## ማስፈራራት

በሕፃናት አስተዳደግ ሌላ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠውና ልዩ ጥንቃቄ ልናደርግበት የሚያስፈልገው ጉዳይ ማስፈራራትን ነው።

በምንም መልኩ ቢሆን ሕፃናት እግዚአብሔርንም ሆነ የቤተክርስቲያን አባቶችን እንዲፈሩ ልናደርጋቸው አይገባም:: «በአንተ ምክንያት እግዚአብሔር ይቆጣል...» «ያንን ካደረክ እግዚአብሔር ይጠላሃል» ወይም ደግሞ « ይኸንን ከፈፀምክ እግዚአብሔር ወደ ሲኦል ያወርድሃል» በማለት በሕፃናት አእምሮ ውስጥ የፍርሃት ናዳ ልንከምር አይገባም:: በሕፃናት ዓይን እግዚአብሔርን የፍርሃት ተምሳሌት፣ ምሕረት አልባ፣ ጨካኝና በነፃነታቸው ፊት የቆመ ባላንጣ አድርገን ልንስልባቸው አይገባም:: በምንም መልኩ እና በማናቸውም ምክንያት ሕፃናትን በእግዚአብሔር ዘንድ በወንጀል ተጠያቂ ሆነው እንዲሰማቸው ማድረግ የለብንም:: ወይም ሕፃናት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት በረጅም የስጋት ወይም የፍርሃት ሰንሰለት የታሰሩ መስሎ እንዲሰማቸው ልናደርግ አይገባም::

የዚህን ጉዳይ ክብደት በሚከተለው ምሳሌ ለማየት ብንሞክር ስለጉዳዩ አስከፊነት ጥሩ አስረጅ ይሆናል:: በአንድ ወቀት አባት በጠና ይታመምና የአልጋ ቁራኛ ይሆናል:: የዚህን ከሞት አፋፍ የደረሰ አባት ስቃይ ያይ ዘንድ ተገቢ አልመሆኑን በማመን የበሽተኛው ልጅ ወደ ዘመዶች ተልኮ እዚያው እንዲቆይ መላ ቤተሰቡ ሁሉ ይስማማል:: አባቱ ከሞተ ሁለት ሣምንት በኋላ ልጁ ወደ ቤቱ ይመለሳል:: ሕፃኑም አባቱ የት እንዳለ ቤተሰቦቹን ሲጠይቅ « እግዚአብሔር ወሰደው» የሚል ምላሽ ይሰጡታል:: በዚህ የተነሣ ልጁ በጣም ይበሳጫል በእግዚአብሔር ላይ ለረጅም ጊዜ የቆየ ምሬት ያድርበታል:: እንደምን እግዚአብሔር አባቱን ነጥቆ ወስዶ የሚወደውን የአባቱን ፍቅር ይከለክለዋል?

በመሠረቱ ልጁ ስለ አባቱ ሞት የተነገረው አግባብ ባልሆነ መንገድ ነው:: ከዚህ ይልቅ «አባትህ ወደ ገነት ገብቷል» በማለት መንገር ይችሉ ነበር::

## ሕፃናትን የሚያሳስባቸው ጉዳይ

በሕፃናት ዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ እነርሱን የሚያሳስባቸውና ትኩረታቸውን የሚስበው ጉዳይ እኛ ከምናስበውና እንዲሆን ከምንፈልገው በጣም የተለየ ነው::

ይህን አስመልክቶ በአስተማሪነቱ ጉልህ ሥፍራ የሚሰጠውና ከሕፃናት ጋር በሚኖረን መስተጋብር በተግባራዊነቱም ሆነ በመሠረታዊ ስልት አስጨባጭነቱ ሊጠቀስ የሚገባ አንድ ጥሩ ገጠመኝ አለ::

በአንድ ወቅት እናት ሕፃን ልጃቸውን አስከትለው አንድ አባት ለመጠየቅ ይሄዳሉ:: እናም በወቅቱ እናትየዋ የልጁን የማስታወስ ችሎታ ቀጳሱ እንዲያውቁ ለማድረግ «ለብፁዕ አባታችን»...«አባታችን ሆይ» የሚለውን መዝሙር ዘምርላቸው በማለት ግፊትና ጫና ያሳድሩበታል:: ሆኖም የሕፃኑ ትኩረት ሌላ ነበር:: የዋህነትና ደስታ በተሞላበት ሁኔታ ወደ ቀጳሱ እየተመለከተ «አዲሱን ቀዩን ጫማዬን አየኸው?» ሲል ቀጳሱን ይጠይቃቸዋል::

በርግጥም ሕፃኑ በአዲሱ ጫማው ልዩ ኩራትና ደስታ ተሰምቶት መላ ትኩረቱን ያደረገው በዚህ ላይ ነበር:: በመሆኑም በዙሪያው ያሉ ሰዎች ሁሉ ያደረገውን ጫማ ተመልክተው በማድነቅ የደስታው ተካፋይ እንዲሆኑ ነበር የእርሱ ፍላጐት:: ምንም እንኳ እናቱ ሕፃኑ መንፈሱን ወዳላዘጋጀበት መንፈሳዊ ድባብ እንዲያተኩር ሊያደርጉት ቢሞክሩም እሱ ግን በራሱ ስሜትና ፍላጐት ነበር የተዋጠው:: ይህን ሁኔታ በጥልቀት ያስተውሉ የነበሩት መንፈሳዊ አባት /ጳጳሱ/ ከዚያች ቅፅበት ጀምሮ አንድ ትምህርት እንዳገኙ በማዘከር ምንጊዜም አንድ ሕፃን ሲገጥማቸው መጀመሪያ የሚያደርጉት ስለልብሶቹ አሰፋፍ፣ ስለቀለሙ ውበትና ዲዛይን አድናቆታቸውንና ሙገሳቸውን መለገስ እንደሆነ ይናገራሉ:: ለምሳሌ:- ያጋጠመቻቸው ሴት ሕፃን ልጅ ከሆነች ለጆሮ ጉትቻዋ ወይም ለፀጉር ጌጧ አልያም ደግሞ ስለያዘችው አሻንጉሊት ተወዳጅነት በአድናቆት እንደሚያናግሯት ያወሳሉ::

በአጠቃላይ ከዚህ በመነሣት ሕፃናት ሲያጋጥሙን «ሚሚ፣ ማሙሽ... ወዘተ» ብለን በመጥራት የተለያዩ ስጦታዎችን በማበርከት ልናስደስታቸው ይገባል::

በቅድሚያ ይህንን ፍላጐታቸውን ካሟላንላቸውና ካስደሰትናቸው በኋላ የመንፈስ ዝግጅት ስለሚኖራቸው እና ዙሪያ ገባቸውን በፍቅር ስለሚመለከቱ የተማሩትን ማናቸውንም መዝሙር እንዲዘምሩልንም ሆነ እንዲነግሩን ልንጠይቃቸው እንችላለን::



## መስጠትና መስጠትን ማስተማር

በመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት ሕፃናት የፍቅር ፍልስፍና ምን ማለት እንደሆነ አይረዱም:: ለእነርሱ ፍቅር ማለት ትርጉሙ መስጠት ማለት ነው::

እግዚአብሔር አምላክ ስለሚወደን ሁሉንም ነገር ሰጥቶናል:: ሌላው ቀርቶ ወላጆቻችን እንኳ ከእግዚአብሔር የተበረከቱልን ስጦታ ናቸው:: እናም ለሕፃናቱ ያለንን ፍቅር ስንገልጽ አንዳች ስጦታ አበረከትን ማለት ነው::

እርግጥ ነው የምናበረክተው ስጦታ እንደ ሕፃናቱ ምርጫ ይለያያል:: እንደ ፍላጎታቸው ጣፋጭ ነገሮችን፣ አሻንጉሊቶችን ወይም መንፈሳዊ ሥዕሎችን ወይም መስቀል ሊሆን ይችላል:: እነዚህን ማድረግ ባንችል እንኳ ቢያንስ ፈገግታና መልካም የአድናቆት የማበረታቻ ቃላት ልናበረክትላቸው ይገባል::

ለሕፃናት በምናበረክትላቸው ስጦታዎች እንደሚደሰቱ ሁሉ በአንጻሩ መስጠትን እንዲያውቁ ልናስተምራቸው ይገባል:: በአጠቃላይ የሕፃናቱ ሕይወት በመቀበል ብቻ የተሞላ ከሆነ ጥሩ አይሆንም:: ስለዚህ መስጠትን ተግተው እንዲማሩ ማድረግ የዘወትር ተግባራችን ሊሆን ይገባል:: ስጦታን ልናስተምር ከምንችልባቸው መንገዶች የሚከተሉት ይገኙባቸዋል::

- እንግዶች በሚኖሩን ወቅት ጣፋጭ ነገርችን የምናቀርብ ከሆነ በእኛ ፈንታ ሕፃኑን ጠርተን «ይህንን

ስእንግዶቻችን ስጥልን» ብለን እንዲያድል ብናደርግ ሕፃኑ ደስታና እንግዶችን በሚገባ ተቀብሎ የሚያስተናግድ ሰው ስሜት ይሰማዋል።

- በምግብ ጠረጴዛ ዙሪያ እስታዊ ምግብ ሲቀርብ ተመሳሳዩን ማድረግ ይቻላል።
- ከእንቶቹና ወንድሞቹ ጋር በሚኖረው እስታዊ ግንኙነት መስጠትን እንዲማር ልናበረታታው እንችላለን።
- የሕፃኑ እናት የሚከተለውን እንድትለው ማድረግም ሌላው ሕፃኑ መስጠትን እንዲያውቅ የማስተማሪያ ዘዴ ነው። «አባባ እስኪመጣ ድረስ ይህንን አንተ'ጋ አስቀምጥና፣ አባባ ሲመጣ ትሰጠዋለህ። እርሱም ባንተ ደስ ይለዋል። ደግሞም ያመሰግንሃል።»
- ምንጊዜም ሕፃኑ ለሰዎች ስጦታዎችን ሲያበረክት ምስጋናና ማበረታቻ መለገስ።
- በተጨማሪም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወይም በቅዱሳን ሰዎች ታሪክ ውስጥ ስጦታን ስለማበርከት የተጻፉ አያሌ ታሪኮችን ማስተማር።

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ የስጦታ ማስተማሪያ መንገዶች ሕፃናት ፍቅርን፣ ማኅበራዊ ኑሮንና ስጦታን የማበርከት በጎ ባሕልን እንዲያውቁ የሚረዱና ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ናቸው።

## የማስታወስ ችሎታ

ሕፃናት በተፈጥሮ ፈጣንና የማስታወስ ችሎታቸውም ያን ያህል የሚበረታ ነው። አዳዲስ ነገሮችን ለማስታወስ



ንቁ ናቸው። ሕፃናት እያደጉ ሲሄዱ፣ ከማኅበረሰቡ ሲቀላቀሉና ወደ ትምህርት ዓለም ሲገቡ አዳዲስ ሃሳቦችና ከተለያዩ ቋንቋዎች የተገኙ አዳዲስ ቃላትን ወደ ጭንቅላታቸው ያስገባሉ ያስታውሷቸዋልም። በዕድሜ እየበሰሉ ሲሄዱ ሁሉንም ነገር ጭንቅላታቸው ላይቀበልና መርሳት ይጀምሩ ይሆናል። ይህ ሁኔታ እርግጥ ድንግል የማስታወስ ችሎታ ይዘው ለተወለዱት ሕፃናት ተፃራሪ ነው።

አንድ የትምህርት ሊቅ በአንድ ወቅት እንደተናጋሩት:- ሕፃናት በተወለዱ በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ውስጥ ባሉት ጊዜያት አንድ ሙሉ መዝገበ ቃላት ማስታወስ የሚያስችል አቅም አላቸው። ሲወለዱ ስለቋንቋ ምንም ነገር የማያውቁት ሕፃናት የንግግር ቃላትን፣ በአከባቢው የሚገኙ ነገሮችንና ስሞችን ወዘተ እየተማሩና እያወቁ ይሄዳሉ። በመሆኑም በዚህ አጋጣሚ ሕፃናት ያሉበትን የማስታወስ ችሎታና የዕድሜ ደረጃ በመጠቀም ለእነርሱ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ማስታወስ እንዲችሉ ልናደርግ ይገባል።

ለምሳሌ:- ቅዳሴያትንና ዝማሬያትን እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስና የቅዱሳን ሰዎች ታሪኮችን ማስታወስ እንዲችሉ ልናስተምራቸው እንችላለን።

ምንም እንኳ ሕፃናት ትርጉሙ ሙሉ በሙሉ ግልጽ ሆኖላቸው ባይረዱትም ጸሎታትን እንዲያስታውሱ ልናስተምራቸው ይገባል። ትርጉሙን የመረዳት ጉዳይ ኋላ

ላይ የሚመጣ ነገር ነው:: ቅድሚያ የሚሰጠው ማስታወሱ ይሆናል:: ለምሳሌ «ጸሎተ ሃይማኖት» እና «አባታችን ሆይ» የመሳሰሉትን ጸሎታት ብናስተምራቸው ትርጉሙን የማስረዳቱ ጉዳይ ቀስ በቀስ ይሆናል::

በሕፃናት ሕይወት ውስጥ ይህንን የዕድሜ ክልል በመጠቀም የማስታወስ ችሎታን ከማስተማር ቸል የሚል ማንኛውም የሰንበት ት/ቤት ወይም የአፀደ ሕፃናት መምህር አጋጣሚውን በከንቱ እንዳባከነ ይቆጠራል::

በተመሳሳይም በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት ልጆቻቸውን «ዛሬ የነገርኳችሁ እነዚህ ቃላት በልቦናችሁ ያድራሉ፣ በቤታችሁም ሆናችሁ ልጆቻችሁን ታስተምሯቸዋላችሁ::» በማለት ጌታ እግዚአብሔር ያዘዘውን ትእዛዝ ከመፈፀም ወደ ኋላ የሚሉ ወላጆችም እንዲሁ አጋጣሚውን መጠቀም ባለመቻላቸው ተወቃሽ ከመሆን አያመልጡም::

ምንጊዜም ቢሆን ማወቅ ያለብን የልጆቻችንን አእምሮ በበጎ ነገር ካልሞላነው በሌሎች ነገሮች መሞላቱ የማይቀር መሆኑን ነው:: የልጆቻችን አእምሮ በመዝሙርና በምስጋና ካልተሞላ ከሌላ አቅጣጫ በተገኙ አልባሌ ነገሮች ይሞላል:: የልጆቻችን አእምሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙ ቅዱሳን ሰዎች ታሪክ ካልተሞላ በብዙ ከንቱና እንቶ ፈንቶ ታሪኮች እንዲሁም ጎጂ በሆኑ ልማዶች መሞላቱ አይቀርም::

እንዲያውም ሁላችንም በቤታችን ውስጥ የመዝሙር



ግጥሞችን የያዙ ፍሬሞችን በግድግዳ ላይ በማንጠልጠል ለሕፃናቱ የመዘመሪያ ፕሮግራም አውጥተን እንዲዘምሩ ብናደርግ ሕፃናቱ በየጊዜው አስታውሰው እንዲዘምሩ ከማስቻሉም በላይ ችሎታቸው እንዲዳብር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል::

የሕፃናት በቤት ውስጥ መኖር ለመላው ቤተሰብ በመንፈስ መባረክ ነው:: /መዝ. 126÷3/ ምክንያቱም በሕፃናት አማካኝነት መላው ቤተሰብ መንፈሳዊ መዝሙሮችን የማድመጥና የመዘመር ዕድል ያገኛል:: መላው ቤተሰብ ወደ መዝሙሩ ይበልጥ በማትኮር መዝሙር መዘመርን በማዘውተር በመንፈሳዊ ሕይወት ይጎለምሳል::

## ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችና በዓላት

ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ጠብቃ ያቆየችው መንፈሳዊ ሥርዓቶች፣ በዓላትና ንዋየ ቅዱሳት ምንኛ የተዋቡና በሕፃናት ልብ ውስጥ ዘልቀው የሚገቡ ብሎም መንፈሳዊ ጸጋን የሚያጎናጽፉ ናቸው::

እስኪ የጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ሀብቶች የሆኑትን ቅዱሳን ሥዕሎች፣ ቅዳሴና መዝሙራት፣ እጣን ሞገሩን እናስብ:: ምንኛ ለመንፈስ እርካታን፣ ለልቡና ሐሴትን ያጎናጽፋሉ:: የካህናቱ አልባሳት እንዲሁም ሽብሸባና ወረባቸው፣ በሥርዓተ ቅዳሴና በወንጌል ንባብ ወቅት የሚንቦገቦገው የሚፍና የሻማ ብርሃን ሥርዓት ስግደቱ

ወዘተ የሕፃናትን መንፈስ እርካታ እንደሚሞሉ ማሰብ ብቻ ሐሴትን ያላብሳል።

በመሆኑም ገና በልጅነትና በአበባነት ዕድሜያቸው የቤተክርስቲያንን ደጃፍ እንዲሳለሙ፣ ትምህርተ ወንጌል እየተመገቡ እንዲያድጉ የተደረጉ ሕፃናት፤ ብሎም በፍላጐታቸው ለዲቁና የተሾሙ ብላቴናዎች የቤተክር ስቲያንን መንፈሳዊ ቅድስና ተካፋይ ከመሆናቸውም ባሻገር በጥልቅ መንፈሳዊ እንዲሆኑ ማስቻሉ ታላቅ በረከት ነው።

እነዚህ በዓላትና መንፈሳዊ ሥርዓቶች በሕፃናቱ ልቦና ውስጥ ጠንካራና ጥብቅ የእምነት መሠረት የሚተክሉ በመሆናቸው ሕፃናት ካደጉ በኋላም ቢሆን ከውስጣቸው ለቅጽበት እንኳ ሊጠፉ አይችሉም።

ሕፃናቱ ቀሚስ ለብሰው ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ፣ ጧፍና ሻማውን ይዘው ካህናቱ የሚያደርሱትን ጸሎት ተከትለው እነርሱም ሲጸልዩ...የቅዱስ ቁርባን ተካፋይ ሲሆኑ እጅግ ደስ ያሰኛል።

ሃይማኖታዊ በዓላት ሥርዓቶች ብቻ ሳይሆኑ በውስጣቸው ጠንካራ እምነትን በፅኑ የያዙ ቀኖናትንና መንፈሳዊ ጸጋዎችን እንዲሁም ተግባራዊ ዕውቀቶችን ሁሉ ያካተቱ ናቸው።

በመሆኑም የሕፃናት አእምሮ በማንኛውም ነገሮች ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት ግድ በሚላቸውና ሁሉንም ነገር በተቃውሞ ለመከራከር ዝግጁ በሚሆኑበት የዕድሜና የብስለት ደረጃ ላይ ከመድረሳቸው አስቀድሞ ለሁሉም



ነገር ታዛዥ በሚሆኑበት የዕድሜ ደረጃ ላይ ሳሉ የዶግማንና የቀኖናን ትምህርት በሙሉ ልንሰጣቸውና እነሱም ሊቀበሉን ይችላሉ። ስለዚህ በልጅነት ዕድሜያቸው የእምነት መሠረት ካላስጨበጥናቸው በአእምሮ ሲበስሉ በምንሰጣቸው ትምህርተ ሃይማኖት እንዲጠራጠሩ ያደርጋቸዋል። በተጨማሪም በሕፃናት ውስጥ የሚያድረውን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንዲቀዳጁ አስተዋፅኦ ስላለው ቸል ልንል አይገባም።

እዚህ ላይ መናፍቃን «ሕፃናት ካደጉና ካመኑ በኋላ ነው ማስጠመቅ የሚኖርብን» ብለው የሚያምኑትና የማይገነዘቡት ነገር ቢኖር ሕፃናትን ከቤተ ክርስቲያንና ከዕለት ተዕለት የመንፈሳዊ ሕይወት ኅብረት እንዳገዷቸው ነው። ሕፃናት ሲያድጉ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ አናውቅም። ወይም ሲያድጉ በእምነታቸው ላይ ጋሬጣ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች እንደሚገጥሟቸው ምንም የምናውቀው ነገር የለም። ስለዚህ ሕፃናትን ከልጅነት ጀምሮ በመንፈሳዊ ሕይወት ኮትኩተን ልናሳድጋቸው ይገባል።

# ክፍል ሁለት

## ከፍተኛው የልጅነት ደረጃ

**ከፍተኛው የልጅነት ደረጃ የሕፃናት ስምንት ተከታታይ ዓመታትን የሚሸፍን ሲሆን ይህ ወቅት በግምት የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ቤት ሕይወትን ያካትታል፡፡**

### በመጀመሪያዎቹ የልጅነት ዓመታትና በከፍተኛ ልጅነት ደረጃ መካከል ያለው ልዩነት

በመሠረቱ እንደ መነሻ ወይም መቅድም በነዚህ በሁለቱ የዕድሜ ክልሎች መካከል የሆነ ወሰን ወይም ምክፈያ ቦይ ማበጀት እንደማይቻል ይታመናል፡፡ በተለይም ሁሉንም ሕፃናት በተመለከተ የመጀመሪያው የልጅነት ጊዜ በዚህ ጊዜ አልቆ የከፍተኛ ልጅነት የዕድሜ ደረጃ ሕፃኑ ይህን ያህል ዓመት ሲሞላው ይጀምራል ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም በብዙ ሕፃናት ላይ ሁኔታዎች ልዩነቶችን ሲፈጥሩ ተደጋግሞ ስለሚታዩ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ አስፍተን ስናየው ሁኔታው ከሕፃናት ሕፃናት የተለያየ እንዲሆን ከሚያደርጉት ነጥቦች መካከል የሕፃናቱ የአስተሳሰብ ደረጃ፣ ብስለት፣ አስተዳደግ፣ በዘር የሚወረሱ ባሕርያትና ሕፃናቱ የሚያድጉባቸው አካባቢያዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች በግምባር ቀደምነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ሁሉ በሕፃናቱ ሁለንተናዊ ሕይወት ላይ የራሳቸውን ተፅዕኖ የሚያሳድሩና በተለያዩ ሕፃናት መካከል የተለያዩ ስሜቶችን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

ከላይ የዘረዘርናቸው ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው ለተነሳንበት ዓላማ አጠቃላይ ሕግ ወይም መመሪያም ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ፤ በብዙዎች ዘንድ እንደ ደረጃ ምደባ በመታየት የተሰነዘሩ አስተያየቶችን መቃኘቱ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

ከፍተኛ የልጅነት ጊዜ የሚባለው የዕድሜ ክልል ብዙዎች እንደሚሉትና እንደሚስማሙት ከ7 ዓመት እስከ 11 ዓመት ያለውን የዕድሜ ክልል ያካትታል:: ይህ የዕድሜ ክልል የመጀመሪያው የትምህርት ቤት ዓመታት በመባልም ይታወቃል:: ይህ ወቅት ሕፃናት ወደ አንደኛ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የሚሄዱበት ወቅት ነው:: ይህን የዕድሜ ክልል ከአካላዊ ዕድገት አኳያ ስናየው ሕፃናቱ የተረጋጋና ቀስ እያለ የሚሄድ የዕድገት ደረጃ የሚያሳዩበት ወቅት ነው:: በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች የአካልም ሆነ የአእምሮ ዕድገት ልዩነት እንደማይታይባቸው ይነገራል::

በዚህ ከፍተኛ የልጅነት ዕድሜ ክልል ውስጥ ጎልተው የሚታዩ አይነተኛ የዕድገት ባሕርያት:- ማኅበራዊ ተግባቢነትና ጓደኝነት የመመሥረት ዝንባሌዎች፤ ታዛዥ ያለመሆን ፍላጎትና አንዳንዴም በነገሮች ያለመስማማት ዝንባሌ ሊከሰት እንደሚችል ይታመናል::

በመሠረቱ የመጀመሪያዎቹና ከፍተኛ የሕፃንነት ዓመታት የዕድሜ ደረጃዎች ብለን በከፋፈልናቸው ወቅቶች ውስጥ ለውጥ በዝግታ የሚከናወንበት፤ የሰብዕናና የአእምሮ ብስለት ምልክቶች የሚታዩበት ከመሆኑም ባሻገር ይህ የአእምሮ ብስለት በአንዳንድ ሕፃናት በጣም ፈጣን ሆኖ ሲከሰት በሌሎች ደግሞ ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል:: በተጨማሪም መዘንጋት የማይኖርብን የተለያዩ ባሕርያት መኖራቸውን ነው:: አንዱ ሕፃን በተፈጥሮ መስህብነት



ያለው፤ ሌላው ደግሞ በቀላሉ ከእኩዮቹ ጋር መግባባት የሚችል፣ ሌላኛው ደግሞ በማኅበራዊ ሕይወት ደካማና በቀላሉ ጓደኛ ማፍራት የሚሳነው ሊሆን ይችላል::

የመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት እና ከፍተኛ ሕፃንነት የዕድሜ ደረጃዎች በጋራ የሚጋሯቸው ባሕርያት አሏቸው:: ከነዚህም መካከል የማስታወስ ችሎታ፣ የማስ ላሰል ወይም የመኰረጅ ዝንባሌ፣ ቀልዶችን የማፍቀር ዝንባሌ በጣም ይስተዋላሉ:: በተቃራኒው ደግሞ የብስለትና የአስተሳሰብ ደረጃ ልዩነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ አይካድም::

## ዕሴቶች

በት/ቤት ዓመታት የዕድሜ ደረጃ ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት የሚሰሟቸውን ነገሮች ሁሉ የማመን ዝንባሌ የሚያሳዩ ቢሆንም እያደጉ ሲሄዱ የተወሰኑ ነገሮችን በመቀበል ሌሎች ሁኔታዎችን በጥያቄ ምልክት ውስጥ በማስገባት የተወሰኑትን ደግሞ የመቃወም አዝማሚያ ያሳያሉ:: ለሕፃናቱ ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች መብራራትና ግልጽ መሆን እንደሚኖርባቸው ይሰማቸዋል::

ሕፃናት በመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት የዕድሜ ክልል ውስጥ በነበሩበት ወቅት ማንኛውም ነገር የእነርሱ መስሎ ይሰማቸዋል:: የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ የመውሰድ መብት እንዳላቸው አድርገው ይቆጥራሉ:: ወደ ከፍተኛ የሕፃንነት የዕድሜ ክልል ሲገቡ ግን የነርሱ የሆነውንና የሌሎች የሆኑትን ንብረቶች መለየት ይጀምራሉ::

ምናልባት እንኳ የሌሎችን ንብረት ወስደው ከሆነ ስህተት እንደሠሩ ስለሚሰማቸው ይህንን ስህተታቸውን ለመደበቅ የሚጥሩበት ጊዜ ነው፡፡ በመሆኑም ስለወሰዷቸው ነገሮች ሲጠየቁ ሊዋሹ ይችላሉ፡፡ አሁን የሚዋሿቸው በመጀመሪያዎቹ የሕፃንነት ዓመታት ወቅት እንደነበሩት ሕልማዊ አይነት የዋሕ ውሸት አይደለም፡፡ የወሰዱትን ዕቃ እንዲመልሱ ቢጠየቁ እንኳ ሊቃወሙ ሊያኮርፉ በጭራሽ ምንም ነገር ላይናገሩና ሊያለቅሱ ሁሉ ይችላሉ፡፡

## ማኅበረሰብ

ይህ የከፍተኛ ሕፃንነት የዕድሜ ደረጃ ሕፃናቱ በቅርብ በቤታቸው ያውቁት ከነበረው ቤተሰብ ወጣ ብለው በውጭ ከሚያገኙት ማኅበረሰብ ጋር የሚቀላቀሉበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሕይወታቸውም በብዙ መልኩ ከሌሎች ሰዎች ጋር ይገናኛል፡፡ ከቤተሰብ እና በቅርብ ያውቋቸው ከነበሩት ሰዎች ባሻገር የሚገጥሙት የት/ቤት ጓደኛና መምህራን በሕፃናቱ አስተሳሰብ ላይ የበኩላቸውን ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ በመሆኑም በነዚህ ሁኔታዎች አማካኝነት ሕፃናቱ እንግዳ ለሆኑ ድርጊቶችና ላልተለመዱ ባሕርያት ይጋለጣሉ፡፡

ይህ ወቀት ወሳኝ በመሆኑ ተገቢውን ጥበቃና ልዩ እንክብካቤ ማድረግ ተቀዳሚ ተግባራችን ሊሆን ይገባል፡፡

ሕፃናት ወደ ማኅበረሰብ ከመቀላቀላቸው አስቀድሞ በቤተሰብ አካባቢ ብቻ በመወሰን በሚቆዩባቸው ወቅቶች የተወሰኑና ጠቀሚታቸው የጎላ መመሪያዎችን በአእምሮአቸው አስቀድመን ልናሰርጽ ይገባናል፡፡ እነዚህ



መመሪያዎች ሕፃናት ወደ አዲሱና ሰፊው የማኅበረሰብ ክፍል ሲቀላቀሉ ሊገጥሟቸው የሚችሉትን ማናቸውንም እንግዳና ያልተለመዱ ክስተቶችን በፈቃደኝነት ለማስወገድ የሚያስችሏቸው ይሆናሉ፡፡ ወይም ደግሞ ከውጭ ሊገጥሟቸው ከሚችሉ እንግዳ ከሆኑና ስህተት ከተሞሉ ድርጊቶች እንዲጠበቁ ጥንቃቄ የተሞላበት ክትትል በማድረግ ከስህተት ልናርማቸው ይገባል፡፡

ሕፃናትን እንደ ልጆቻችን ብቻ ሳይሆን እንደጓደኞችን አድርገናቸው ሁሌም የደኅንነት ዋስትና የምንሰጣቸውና ለሚፈጽሟቸውም ስህተቶች ተገቢውን ትኩረትና እውነተኛ የምክር አገልግሎት በመስጠት ምንም አይነት ጉዳት እንደማይደርስባቸው እንዲያውቁ ካደረግን የሚገጥሟቸውን ነገሮች ሁሉ ሳይሸሽጉ ሊነግሩን ስለሚችሉ ማናቸውንም ነገሮች እንዴት አድርገው ሊቆጣጠሯቸውና ሊይዟቸው እንደሚገባ እያስረዳናቸው ከማኅበረሰቡ ጋር እንዴት ተጣጥመው መዝለቅ እንደሚችሉ መንገድ ልንከፍትላቸው እንችላለን፡፡

## የሰንበት ት/ቤቶች

ሕፃናት በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ዕድሜ ክልል ውስጥ በሚደርሱበት ወቅት ሃይማኖታዊ ትምህርት ወደሚያገኙበት ሰንበት ት/ቤት ይገባሉ፡፡ አንዳንድ ቤተሰቦችም የሕፃናቱን ትምህርት በተመለከተ ሙሉ በሙሉ ኃላፊነቱን በሰንበት ት/ቤት ላይ ሲጥሉ ይታያል፡፡ ነገር ግን የሕፃናትን ሃይማኖታዊ ትምህርት

በተመለከተም ሆነ አጠቃላይ የሕፃናቱን ቁጥጥር በሰንበት ት/ቤት ላይ ብቻ መጣል ከፍተኛ ስህተት ነው::

ለመሆኑ የሕፃናቱን ሃይማኖታዊ ትምህርት በተመለከተ ወላጆች ሊያደርጉት የሚገባው የቁጥጥር ተግባር ምን መሆን አለበት?

በመሠረቱ ለሕፃናት ሰንበት ት/ቤት መሄድ በጣም ቀላል ሲሆን በሰንበት ት/ቤቱ ውስጥ የሚሰጡትን ትምህርቶች ባግባቡ ላይከታተሉና ላይገነዘቡ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች አሉ:: ብዙውን ጊዜ ከተግባርና ከልምድ እንቅስቃሴ እንደተገነዘብነው ከሆነ በሰንበት ት/ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ብዙ ሕፃናት ስለተማሩት ትምህርት ሲጠየቁ «አላውቅውም፣ እኔጃ ወይም አላስታውሰውም አልያም ትምህርቱን አልተከታተልኩም ነበር» የሚል ምላሽ ሲሰጡ ይስተዋላል::

እርግጥ ነው የሰንበት ት/ቤት መምህራን ሕፃናቱ የተሰጠውን ትምህርት በአግባቡ መከታተላቸውንና በርግጥም ተረድተውት እንደሆነ ሊቆጣጠሩ ይገባል:: ከመምህራን የቅርብ ክትትል በተጨማሪ ወሳኝ የሚሆነው የወላጆች ጥብቅ የሆነ ክትትል ነው:: ሕፃናት ከት/ቤት ሲመለሱ ወላጆች ስለተማሩት ትምህርት ሊጠይቋቸው ይገባል:: እናም ሕፃናት ሁሌም ከት/ቤት መልስ ስለተማሩት ትምህርት በወላጆቻቸው እንደሚጠየቁ ስለሚያውቁ ለትምህርቱ ትኩረት መስጠት ይጀምራሉ:: ሲጠየቁ «አላውቅም» የሚል ምላሽ አይሰጡም::



በተጨማሪም ወላጆች የሕፃናቱን ዕውቀት ለማጎልበት እነርሱም የእምነት ሰዎች መሆናቸውን እንዲረዱ በቤት ውስጥ ተጨማሪ ትምህርት ሊሰጧቸው ይገባል:: ሕፃናት ስለመጽሐፍ ቅዱስና ስለሌሎች መንፈሳዊ ጉዳዮች አንዳንድ ነገሮች ሲቸግሯቸው ቤተሰቦቻቸውን ሊጠይቁ ይችላሉ:: በዚህም ለእነርሱ አክብሮት ይኖራቸዋል::

ሕፃናት ባሉበት በዚህ የዕድሜ ደረጃ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ለመቀበልም ሆነ ለማስተማር በጣም ቀላል ነው:: ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሕፃናቱ የሚገኙበት የዕድሜ ደረጃ ነገሮችን በቀላሉ ለመቀበል የሚያስችል በመሆኑ ነው:: ስለዚህ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሕፃናት ወደ ጥርጣሬና እርግጠኛ አለመሆን ሁኔታዎች ውስጥ ስለማይገቡ መንፈሳዊ ትምህርቶችንም ሆነ ሌሎች በጎ አመለካከቶችን ልናስተምራቸው የሚገባ ወቅት መሆኑን አበክረን ለመግለጽ እንወዳለን::

## መንገር

በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት የምንነግራቸውን ነገሮች ለመቀበል ዝግጁ ናቸው:: የምንሰጠውን ማናቸውንም መረጃ ሁሉ ያለተቃውሞ ይቀበሉናል:: እርግጥ ተቀባይነት የሌላቸውንና እንደቀልድ የሚቆጠሩ ነገሮችን ላይቀበሉ ይችሉ ይሆናል::

በመሆኑም በሕፃናት አእምሮ ውስጥ የሃይማኖት መሠረትን ለመትከል ምቹ ጊዜ ይህ ወቅት በመሆኑ ሕፃናት መማር የሚገባቸውን ነገር ቀለል ባለ የማስተማር

ዘዴ ልናስተምራቸው ይገባል:: የምናስተምርበት መንገድ ማብራሪያ ያለውና ትንታኔን መሠረት ያደረገ መሆን አይኖርበትም:: ይህንን መንገድ ከተጠቀምን ሕፃናቱ ይደናገራሉ::

ስለዚህ በቀላል /በመንገር/ የማስተማር ዘዴ ልናስተምራቸው እንችላለን:: ለምሳሌ:- ምሥጢረ ሥላሴን፣ ትእምርተ መስቀል ሠርቶ እንዴት እንደሚያማትቡ ብናስተምራቸው በቀላሉ ይረዱናል:: እንዲሁም «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ» ብለን ብንነግራቸው እነርሱም ያለምንም ጥያቄ ደግመው ይሉታል:: በተጨማሪም ስለ «ጸሎተ ሃይማኖት» ብንነግራቸው ስለይዘቱ ለመከራከር ሳይሹ፣ የቃላቱን ትርጉም ሳይጠይቁ በቀላሉ ይቀበላሉ:: ነገር ግን በዚህ በሚገኙበት የዕድሜ ክልል እያንዳንዱን ነገር ለማብራራትና ለመተንተን የምንሞክር ከሆነ አላስፈላጊ ወደ ሆነ ነገር ውስጥ እንዲገቡ እናደርጋለን:: የእነዚህንም ነገሮች ጥልቅ ትርጓሜ ለመረዳት የአእምሮ ብስለት አቅማቸው አይፈቅድላቸውም::

## ተገቢ ትምህርት

ለሰንበት ት/ቤት መምህራን በአፅንኦት ለመምከር የምንሻው ጉዳይ ቢኖር ለሕፃናት የሚሰጡት ትምህርት ዕድሜያቸውን፣ የአእምሮ ብስለት ደረጃቸውንና የአካባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ያደረገ ተገቢ ትምህርት መስጠት እንዳለባቸው ነው::



በአንድ ወቅት አንድ መምህር ተሞክሮአቸውን ሲናገሩ በአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎችን ሲያስተምሩ የመግደላዊት ማርያምን ታሪክ ምሳሌ በማድረግ ለልጆቹ ተግባራዊ ዕውቀት ለማስጨበጥ ሙከራ ማድረጋቸውን ገልፀው ነበር:: /በነገራችን ላይ መምህሩ እንደሚሉት ይህ ሕፃናቱ የሚገኙበት የዕድሜና የክፍል ደረጃ ከልጅነት ወደ ሙሉ ሰውነት መድረክ የመሸጋገሪያ ዕድሜ በመሆኑ በልጆቹ ልቡና ጠቃሚ መመሪያዎችን ለማስረፅ ምቹ ጊዜ በመሆኑ ይህን ዕድሜ በጣም ይወዱታል::/ እናም መምህሩ ማስተላለፍ የፈለጉትን መልእክት ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ የመግደላዊት ማርያምን ታሪክ ይነግሯቸዋል:: ወቅቱ የትንሣኤ በዓል ስለነበር መግደላዊት ማርያም በሌሊት ተነስታ ወደ መቃብር ሥፍራ ትሄዳለች በማለት ታሪኩን ካወጓቸው በኋላ ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ ሁሌም ቢሆን በጠዋት ተነስቶ ቤተክርስቲያን መሄድ አስፈላጊ እንደሆነ ለተማሪዎቻቸው ይነግሯቸዋል:: ስለጉዳዩ በስፋት ገለፃ ካደረጉ በኋላ ተማሪዎቹን «ተግባባን?» ብለው ይጠይቋቸዋል:: ልጆቹም ባንድ ድምፅ መስማማታቸውን ይገልጹላቸዋል:: «እናስ ታዲያ እናንተስ በሚቀጥለው ሳምንት ወደ ቤተ ክርስቲያን በሌሊት ትሄዳላችሁ?» በማለት ይጠይቃሉ::

የሚያሳዝነው ግን ተማሪዎቹ በሙሉ መሄድ እንደማይችሉ ይመልሱላቸዋል:: መምህሩም የማስተማሪያ

መንገዳቸው የተሳካ ባለመሆኑ ያዝኑና ራሳቸውን ይጠይቃሉ:: ስህተታቸውም ምን ላይ እንደነበር ምክንያቱን ለማግኘት ያውጠነጥናሉ:: እናም ተማሪዎቹ ለምን ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ እንደማይችሉ ይጠይቋቸዋል:: ከተማሪዎቹ መካከል አንዱ ተነሥቶ «አሁን ያለንበት ወቅት ትምህርት ቤት የሚዘጋበት ስላልሆነና ለፈተናም እየተዘጋጀን በመሆኑ ማታ ማታ ስናጠና እናመሻለን:: ስለዚህ በጠዋት ተነሥተን ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ አንችልም::» ሲል ይመልስላቸዋል:: ሌላው አምስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተማሪዎችን የሚወክለው ልጅ ተነሥቶ «ሁሌም በጠዋት ተነሥቼ ቤተክርስቲያን መሄድ አልችልም:: ምክንያቱም አባቴ ወደ ቤተክርስቲያን ከረፈደ በኋላ ይዞኝ ስለሚሄድ ነው::» ሲል ይመልሳል:: ሌላው ተማሪ ደግሞ ተነሥቶ «በጠዋት ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ የማልችለው ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት እየተነሣሁ ለቁርስ የሚሆን ነገር እንድገዛ ቤተሰቦቼ ስለሚልኩኝ ነው::» በማለት ይመልስላቸዋል::

በመሆኑም አስተማሪው ያስተማሩት ትምህርት አሳማኝ የነበረ ነገር ግን ልጆቹ ያሉበትን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት እንዳላገኘ ይገነዘባሉ:: እናም ይህ ያልተሳካ የማስተማሪያ መንገድ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳደረሰባቸው ባይክዱም አወንታዊ ውጤት እንዳስከተለ አበክረው ይናገራሉ:: እናም ሕፃናትን በምናስተምርበት ጊዜ ከምንነግራቸው ታሪኮች ጋር በተጓዳኝ የሕፃናቱን አጠቃላይ ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ መሆኑን እርግጠኛ መሆን እንደሚኖርብን ልናስምርበት ይገባል በማለት መምህሩ ልምዳቸውን አካፍለውናል::

ለሕፃናት ትምህርት በምንሰጥበት ጊዜ የትምርቱን ፍሬ ሃሳብ በአራት ክፍለን ለመስጠት እንደምንችል መገንዘብ ያሻል::

1. የትምህርቱን ፍሬ ሃሳብ በማብራራት መንፈሳዊ ትምህርቱን ለይቶ መገንዘብ
2. እነዚህን ትምህርቶች በተግባራዊ ሕይወታችን ውስጥ ለመገልገል መቻል
3. በትምህርቱ አሰጣጥ ሂደት ሊገጥሙ የሚችሉ መሰናክሎችንና ጎጂ ጎኖችን በመረዳት ለማስወገድ መሞከር
4. ክለሳ፣ ጥያቄዎችንና ውይይቶችን በትምህርቱ ፍሬ ሃሳብ ላይ ተመርኩዞ ማድረግ የሚሉት ናቸው::

## ሕፃናት አማንያን ናቸው

ሕፃናት ሲወለዱ እምነትን በውስጣቸው ይዘው ነው:: እምነት በደመ ነፍሳቸው ውስጥ የተከተበ ጉዳይ ነው:: በመሆኑም ስለጸሎት ብንነግራቸው በፍጹም ሊቃወሙ አይችሉም::በሚጸልዩት ጸሎት ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደሚችሉ ብናስተምራቸው «እግዚአብሔር ማን ነው?»...«ለመሆኑ የት ነው ያለው?» ብለው አይጠይቁም:: እናም እምነት ከሕፃናቱ ጋር አብሮአቸው

የሚወለድ አንድ የተፈጥሮ አካል መሆኑን ልንገነዝብ ያስፈልጋል።

መናፍቃን «ሕፃናት እስኪያምኑ ድረስ መጠበቅ ይኖርብናል።» ብለው የሚከራከሩት ይህን እውነት መረዳት ባለመቻላቸው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ይህ ሕፃናቱ የሚገኙበት ከፍተኛ የልጅነት ዕድሜ የእግዚአብሔርን ፍቅር ፣ ለእኛ የሚያደርገውን ጥበቃና እንክብካቤ...ወዘተ ሕፃናት እንዲያምኑ ለማድረግ ጥሩ ወቅት ነው። ለሕፃናት እግዚአብሔር የሁሉም ነገር ምንጭ እንደሆነ ውቧን ፀሐይ፣ ደማቋንና ብርማይቱን ጨረቃ ፣ ኩል መስሎ በተንጣለለው ጥቁር ሰማይ ላይ ብርሃናቸውን የሚያፈነጥቁትን ከዋክብት፣ ዛፎችን፣ በተንጣለለው ሜዳ ላይ የበቀሉትን ለምለም ሣሮችና ማራኪ አበቦችን እንዲሁም የተዋቡትንና የሚያጓጉትን ልዩ ልዩ እንስሳትንና አእዋፍን ሁሉ የሰጠን አፍቃሪ ልብ ያለው አምላካችን እንደሆነ ልናስተምራቸው እንችላለን። በተጨማሪም የምድራችንን ውበት ሁሉ የምናይበትን ዓይን፣ ልዩ ልዩ ጣዕመ ዜማዎችን የምናደምጥበት ጆሮ እንዲሁም ቀን ስንሠራ ውለን እንድንተኛና እንድናርፍ ምሽትን እንደሰጠን ሁሉ ልናስተምራቸው እንችላለን።

ይህ የዕድሜ ክልል ስለእግዚአብሔር ኃያልነትና የነገሥታት ንጉሥነት ለመንገር ምቹና ጥሩ ጊዜ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ያለ፣ የነበረ፣ የሚኖር በሥፍራዎች ሁሉ የሚገኝ እንደሆነ፤ የምናደርገውን ነገር ሁሉ



እንደሚያይ፣ የምንናገረውን ነገር ሁሉ እንደሚሰማ ለመንገር በጣም ጥሩ ጊዜ መሆኑን ማስገንዘብ እንሻለን።

በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት ምድራዊ ወላጅ አባታቸውን ሁሉንም ሊያደርግላቸው እንደሚችል ይሰማቸዋል። እናም ከአባታቸው ጋር ሽርሽር በሚሄዱበት ወቅት «አባባ ይህን መኪና ወይም ይህንን ፎቅ ግዛልኝ?» በሰማይ አይሮፕላን ሲሄድ ካዩ «ወይ አይሮፕላን ግዛልኝ?» ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ። አባትየውም «እሺ ልጄ ስንመለስ አይሮፕላኑን ገዝተን አስጠቅልለን ወደ ቤት እንሄዳለን» በማለት ሊቀልድ ይችላል። ሕፃናቱም የጠየቁትን በኋላ ይረሳሉ።

እንግዲህ ምድራዊው አባት ለልጁ ብዙ ነገር ሊደርግለት የሚችል ከሆነ የሰማይ አባታችንስ እንደምን ከዚህ የበለጠ ድንቅ ነገሮችን አያደርግልንም? ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ «ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም» /ዮሐ. 14÷18/ በማለት ያስረዳል።

በተጨማሪም ሕፃናቱ በሚገኙበት በዚህ የዕድሜ ደረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚገኙት ተአምራት ልንነግራቸው እንችላለን። ለምሳሌ:- ስለ አምስቱ እንጀራና ሁለቱ ዓሣዎች /ማቴ. 14÷15-21/፣ ዓይነ ሥውር ሆኖ ስለተወለደውና በኋላም ዓይኑ ስለበራበት ሰው /ዮሐ. 9÷1-11/፤ የኤርትራን ባሕር አቋርጠው ስለሄዱት እስራኤላውያን /ዘፀአ. 13÷18-22/፣ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት /ሉቃ. 24÷50/ እና ስለ ኤልያስ በእሳት

ሥረገላ መነጠቅ /2ነገ.2÷1-12/ ልናስተምራቸው እንችላለን::

እነዚህ እውነተኛ ተአምራት ለሕፃናት ከዓለማዊ ተረቶች በበለጠ እጅግ በጣም ጠቀሜታ ያላቸው አማናዊ ታሪኮች ናቸው::

## ታሪኮች

የተለያዩ ታሪኮችን ማፍቀርና መመሰጥ የከፍተኛ ሕፃንነት ዕድሜ መለያ ባሕርይ ነው:: በዚህ ዕድሜ ሕፃናት በፊት ከነበሩበት የሕፃንነት ደረጃ በበለጠ ታሪኮችን ማድመጥ ይወዳሉ:: ረጅም ሰዓት የሚወስዱ ታሪኮችን ብንነግራቸው እንኳን የመሰልቸት ሁኔታ አይታይባቸውም:: እንዲያውም ባገኘናቸው ቁጥር ተጨማሪ ታሪኮችን እንድንነግራቸው ይጠይቁናል::

አንድ አባት እ.ኤ.አ በ1963 ዓ.ም ከዚህ ጋር የተያያዘ ገጠመኛቸውን ሲናገሩ በወቅቱ በአንድ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት ጉባዔ ለመካፈል ይሄዳሉ:: እዚያም ላገኟቸው ሕፃናት አንዳንድ ታሪኮችን ይነግሯቸውና በጣም ይደሰታሉ:: በዓመቱ እኚህ አባት በተመሳሳይ ጉባዔ ወደ ዚያው ሰንበት ት/ቤት ሲሄዱ ሕፃናቱ ተሰብስበው ይከቧቸውና ባለፈው ዓመት እንዳደረጉት ሁሉ ሌላ ታሪክ እንዲነግሯቸው ይጠይቋቸዋል::

ይህ የሚያመለክተው በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት ምን ያህል ታሪኮችን መስማት እንደሚወዱ ነው:: አንድ ሕፃን ሰንበት ት/ቤት ሄዶ ሲማር ቢያንስ አንድ



ታሪክ ተነግሮት ካልመጣ በዕለቱ ምንም ዓይነት ትምህርት ቀስሞ እንዳልመጣ ይታሰባል:: በመሆኑም ሕፃናት ታሪኮችን መስማት እንደሚወዱ ሁሉ የሚተርኩላቸውንም ሰዎች በጣም ይወዳሉ:: እንዲያውም ብዙ ጊዜ አባቶችን በሕፃናት እንዲወደዱ የሚያደርጋቸው ይኸው ለሕፃናት ተረቶችንና ታሪኮችን መናገራቸው ነው::

በመሆኑም በሕፃናት ተወዳጅ እንድንሆን ብዙ ታሪኮችን ማወቅና በሚጥማቸው መልኩ መተረክ ይጠበቅብናል:: እናም ለሕፃናት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ታሪኮችን፣ የቅዱሳንን ገድል፣ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ እንዲሁም ጠቃሚ መልእክት እስካላቸው ድረስ የእንስሳትንና አእዋፍን የፈጠራ ታሪኮች ሁሉ ልንነግራቸው እንችላለን::

ታሪኮችን ወይም ተረቶችን በተመለከተ ሕፃናት ብቻ ሳይሆኑ ዐዋቂዎችም ጭምር አዲስና ማራኪ እስከሆኑ ድረስ በተለያዩ ስብከቶችና ትምህርቶች መሐል ሲሰሙ ያስደስታቸዋል::

በከፍተኛ የሕፃንነት ዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት የምንነግራቸው ታሪኮች ጥበብ የተላበሱና የአስቂኝነት ገፅታ ካላቸው ሕፃናት ታሪኩን ደጋግመን እንድነግራቸው ይጠይቁናል::

ስለዚህ ለሕፃናት ጥበብ የተሞላባቸውንና ሳቅን የሚያጭሩ አስደሳች ታሪኮችን ለመናገር ምቹ ሁኔታዎችን መጠቀም እንደሚኖርብን ለመምከር እንወዳለን::

## የሰማዕታት ታሪኮችን የመተረኪያ ዘዴዎች

ሕፃናቱ በሚገኙበት በዚህ የዕድሜ ደረጃ የሰማዕታትን ስቃይና መከራ አጉልተው የሚያሳዩ፣ የተቀበሉትን ፍዳ የሚያወሱትን ታሪኮች መተረክ በፍፁም ለሕፃናቱ ተስማሚ አይሆንም::

በምንም አይነት መንገድ ስሜትን በሚሸነቁጡና መጥፎ ገፅታን በሚያጎሉ ወይም በሚያስጨንቁ ታሪኮች ሕፃናትን በስጋትና ፍርሃት እንዲዋጡ ማድረግ ተገቢ አይደለም:: ሰማዕታት የተቀበሉትን ግፍና በደል የሚያንፀባርቁ ታሪኮችን በቀጥታ ለሕፃናት መተረክ ማለት ሕፃናት የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል ድፍረት እንዲያጡ ማድረግ ብሎም ክርስቲያን ለመሆን የሚያደርጉትንም ትጋት መገደብ ይሆናል:: በመሆኑም ከትረካ ተግባራችን ውስጥ ፍርሃትን የሚፈጥሩ ክፍሎችን ሙሉ በሙሉ አውጥተን ማስወገድ ይኖርብናል::

ከዚህ በኋላ ከአጠቃላይ የሰማዕታት ገድለ ታሪክ ውስጥ የአርበኝነት ተግባራቸውን፣ ድፍረታቸውንና ቆራጥነታቸውን የሚያወሱትን ክፍሎች እንዲሁም የዓላውያን ነገሥታትን ቁጣና ዛቻ የተጋፈጡባቸውን መንገድ የሚያወሱትን ታሪኮች መርጠን በማውጣት ማስተማር ጥሩ ይሆናል:: ለምሳሌ:- ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ በዲዮቅልጥያኖስ ፊት በድፍረት ሲጋፈጥ ወይም ሌሎች ሰማዕታት ለፍርድ ሲቀርቡና ሰማዕት ለመሆን ሲሄዱ ያሰሙት የነበረውን መዝሙርና ምስጋና እንዲሁም በእስር ቤት ውስጥ በቆዩባቸው ጊዜያት የነበራቸውን ድፍረትና ጥንካሬ በጥሩ ሁኔታ ለሕፃናት መተረክ ይቻላል::



በጊዜው ሰማዕታት ራሳቸውን መሥዋዕት ለማድረግ ሲጓዙ ከክርስቶስ ጋር እንደሚገናኙ ያስቡ እንደነበርና ወደ ገነት በማምራት ከመላእክትና ቅዱሳን ጋር እንደሚ ቀላቀሉ እምነታቸው የፀና እንደሆነ የሚያወሱትን ታሪኮች መንገር ይቻላል:: በተጨማሪም ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንዲሞት መርዝ ሲሰጠው በክርስቶስ ትእምርተ መስቀል አማትቦ መርዙን በጠጣው ጊዜ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት መትረፉን የሚያወሳውን ታሪክ መንገርም ይቻላል:: እንዲሁም ቅዱስ ፖሊካርፐስን ለማቃጠል እሳት ባነደዱበት ጊዜ በእግዚአብሔር ከሃሊነት መትረፉን የሚያወሳውን ተአምር መተረክ ጥሩ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ወንጌላዊ ቅዱስ ዮሐንስ የተቀበለውን መከራ፣ እግዚአብሔር ያደረገለትን ጥበቃ ማውሳትም ይቻላል::

ሰማዕታት እኒህን መከራዎች ሲቀበሉ የጠበቃቸውንና ያጠነከራቸውን የእግዚአብሔርን እጅ ለማየት ከመብቃታቸውም በላይ የሰማዕትነትን ተግባር ፈጽመው የድል አክሊልን ተቀዳጅተዋል::

በመሆኑም ሰማዕታት በዚህ ዓለም የሠሩትን ድንቅ ተግባራትና ተአምራት ሁሉ በመተረክ ሕፃናት ሰማዕታትን እንዲያፈቅሩ ማድረግ ከመቻላችንም በላይ በእግዚአብሔር ፊት ያገኙትን ክብርና ሞገስ እንዲሁም የማማለድ ጸጋ

እንዲገነዘቡ ማድረግ ይቻላል።

በተረፈ ግን የቅዱስ ጊዮርጊስን ሰማዕትነት ስቃይና መከራን እንደተቀበለ የሚያወሳውን ታሪክ መተረክ አይኖርብንም። ለሕፃናት እንዲህ አይነት ታሪክ ስንነግራቸው ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል። ምክንያቱም ሕፃናቱ ባሉበት የዕድሜ ደረጃ አሰቃቂ መከራዎችን የሚያወሱ ታሪኮችን ለመቀበል አእምሮአቸው ስለማይፈቅድ ነው። ይህንን ሕፃናቱ በአእምሮና በመንፈሳዊ ሕይወት እያደጉ ሲሄዱ ሰማዕታት እንዴት ራሳቸውን ለስቃይና ለመከራ አሳልፈው እንደሰጡ፤ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሲሉ እንደምን በጽናት ሳይናወጡ እንደቆሙ ልንተርክላቸው እንችላለን።

## ቅጣት

ለልጆች ፍቅር ማሳየት ማለት ከሚገባው በላይ ማሞላቀቅ ማለት አይደለም። እርግጥ ሕፃናት መልካም ተግባራትን ባከናወኑ ጊዜ መሸለም፣ ማሞገስና ማበረታታት የሚገባ ሲሆን ጥፋት ሠርተው በተገኙ ጊዜ፤ በተለይም ደግሞ ጥፋቱ ሌሎችን የሚጎዳና ለማንም ተስማሚ ያልሆነ ድርጊት ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተገቢውን ተግሣፅና ቅጣት ልናደርግ ይገባል። /ምሳ. 22÷6። ቈላ. 3÷21። ኤፌ. 6÷4/

በሌላ መልኩ ሕፃናትን የምናሞላቅቃቸውና በሚጠይቋቸው ጥያቄዎች ሁሉ እነርሱ እንደፈለጉ ምላሽ የምንሰጥ፤ ፈቃዳቸውን የምንፈፅምላቸው ከሆነ ራስ ወዳድነትን እንዲማሩ፣ ስህተት የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ከመፈፀም ወደኋላ እንዳይሉ እናደርጋቸዋለን። ይህ ሁኔታ ደግሞ ሕፃናት በማናቸውም ነገሮች ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የመቻል ደረጃ ላይ ሲደርሱ በጩኸትና በለቅሶ ሊያስፈራሩንና የቤተሰብን አቋም ሁሉ ሊያናጉ ይችላሉ።

በመሆኑም ሕፃናት ጥፋተኛ ሆነው በተገኙ ጊዜ ለቅሶና ጩኸታቸው ምንም ሳያስጨንቀን ተገቢውን ቅጣት ልንቀጣቸው ይገባል። ምክንያቱም ቅጣትን መቀበላቸው ለሕፃናት በመልካም ሥነ ምግባር መታነጽ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በዕብራውያን 12÷6 ላይ የጻፈውን ቃል ማስታወስ ይኖርብናል። «ልጄ ሆይ÷የጌታን ቅጣት አታቅልል ÷ በሚገሥፅህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና÷ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል።»

እንግዲህ የፍቅር ሁሉ ምንጭ የሆነው እግዚአብሔር አምላክ የሚቀጣና የሚገሥፅ፤ እንዲሁም ተግሣፁና ቅጣቱ ከፍቅሩ ጋር የማይፃረር ከሆነ እኛም ልጆቻችንን መቅጣት ይገባናል። ይህም ክፉ በሆነ መንገድ ሳይሆን ሊያስተምራቸው በሚችል ሁኔታ መሆን ይኖርበታል።

በመሆኑም ላጠፉት ጥፋት ተገቢውን ቅጣት ሰጥተን ሥነ ሥርዓት እንዲይዙ ካደረግናቸው በኋላ አሳቢነታችንንና ፍቅራችንን ልናሳያቸው ይገባል። ሥነ ሥርዓት እንዲይዙ ስንል የወሰድነው እርምጃ ፍቅራችንንና

አሳቢነታችንን መለወጣችን ሳይሆን ባጠፉት ጥፋት ላይ የአቋም ለውጥ ማድረጋችን መሆኑን ማሳወቅ ይኖርብናል::

በተጨማሪም በ1ሳሙኤል 3÷13 ላይ ካህኑ ዔሊ ልጆቹ ሲያጠፉ አይቶ ዝም በማለቱ እግዚአብሔር እንደገ ሠፀው ማስታወስ ይገባናል::

በሌላ በኩል ሕፃናትን ርኅራኄ በጎደለውና በክፉ መንገድ ሥነ ሥርዓት ለማስያዝ መሞከር ወደ ጥፋት የሚያመራ የተሳሳተ መንገድ ነው::

በመሆኑም ወላጆች መልዕክት የሚያስተላልፉባቸው፣ የተግሣፅና ቅጣት እርምጃ የሚወስዱባቸው መንገዶች ሁሉ በህዘኔታና በርኅራኄ የተሞሉ መሆን ይኖርባቸዋል:: ከርኅራኄ የራቀ ቅጣት ወይም ተግሣፅ ሕፃናት የወላጆቻቸውን ፍቅርና እምነት የተነፈጉ እንዲመስላቸው ያደርጋል::

## የአካል ቅጣት

በሕፃናት ላይ ከሚፈፀሙ በደሎችና ጉዳቶች መካከል ድብደባ አንዱ ነው:: በአገራችን የሕፃናት አካላዊ ቅጣት ሥር የሰደደ ችግር ነው:: በሕፃናት ላይ የሚደርሱ የቅጣት በደሎችና ጉዳቶች በአብዛኛው ሆን ተብለው ሕፃናቱን ለመጉዳት የሚፈጸሙ ሳይሆኑ ቅጣቶቹ የሚያስከትሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ ባለማወቅና ሥነ ሥርዓት ለማስያዝ በሚል ምክንያት የሚደረጉ ናቸው::

በአንፃሩ ሕፃናት ለእንዲህ ዓይነቱ የአካል ድብደባም ሆነ ለተለያዩ አደጋና ጉዳቶች የሚጋለጡት የራሳቸውን



መብት ለማስጠበቅ የማይችሉና የዕዋቂዎችን እንክብካቤና ጥበቃ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች በመሆናቸው ነው:: ይህ ሁኔታ ለሕፃናት የተለየ አያያዝና ጥንቃቄ በመጠየቁ የዓለም ኅብረተሰብ የሕፃናት መብቶች የሚጠበቁበትን ልዩ ስምምነት (Convention) አጽድቋል:: በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 19 ቁጥር 1 ላይ ሕፃናት በአእምሮም ሆነ በአካል ጉዳት ከሚያስከትል ድብደባ እንደጠበቁ የሚከተለውን አስፍሯል:: « የኮንቬንሽኑ አባል አገሮች ሕፃናት በወላጆቻቸው ወይም በአሳዳጊዎቻቸው ወይም በሌሎች ሰዎች ቁጥጥር ሥር በሚገኙበት ጊዜ ማንኛውም ዓይነት በአካላቸው ወይም በአእምሮአቸው ላይ ስጉዳት ወይም ጉስቁልና የሚደርግ አያያዝ፣ በቸልታ መጣል ወይም መንገላታት፣ ለሰው የሚገባ ክብካቤ ማጣት ወይም የጥቅም ማግኛ መሆን፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ መገደድ ጥምር እንዳይደርስባቸው ተገቢውን የሕግ፣ የአስተዳደር፣ የማኅበራዊና የትምህርት እርምጃዎች ይወስዳሉ::»

በአገራችን ሕፃናት በወላጆችና በአሳዳጊዎች፣ በቤት ሠራተኞች፣ መምህራንና ሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች ይደበደባሉ:: እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ የሕፃናት ጥፋትና ቅጣት ተመጣጣኝ ሆኖ አይገኝም::

ወላጆችና አሳዳጊዎች ልጆችን የሚቀጡት ጠባያቸው እንዳይበላሽ ወይም ለመቆጣጠር ነው:: ይሁን እንጂ ለሕፃናት ጠባይ መለወጥ ምክንያቶቹ ምን እንደሆኑ ስለማያጤኑ ከሌሎች የሥነ ሥርዓት ማስከበሪያ አማራጭ

እርምጃዎች ይልቅ የሚያደሉት ወደ አካል ቅጣት ወይም ድብደባ ነው።

ርዕሳነ መምህራንና መምህራን እንደዚሁም የት/ቤት የጥበቃ ሠራተኞች ተማሪዎችን የሚቀጡት ወይም የሚገርፉት በሥነ ሥርዓት ስም ነው። ተማሪዎች በጠባያቸው ጥሩ፣ በትምህርታቸው የተመሰገኑ ሆነው እንዲያድጉ ለመቆጣጠር ለበጐ ዓላማ ነው። ነገር ግን በቤተሰብም ሆነ በት/ቤት ኃይልን የሥነ ሥርዓት ማስጠበቂያ ማድረግ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን በርካታ ጥናቶች ያስገነዝባሉ። ይህን ችግር ት/ቤቶችም ሆኑ ቤተሰብ ቢገነዘቡ ኖሮ የአካል ቅጣትን እርግፍ አድርገው በመተው በምትኩ በሌሎች የሥነ ሥርዓት ማስጠበቂያ ዘዴዎች ይጠቀሙ ነበር።

ወላጆችና የቤተሰብ አባላት መምህራንና የት/ቤት ማኅበረሰብ የአካል ቅጣት የሚያስከትላቸውን ችግሮች እንዲያውቁና በሌሎች የሥነ ሥርዓት ማስጠበቂያ ዘዴዎች ሥነ ሥርዓትን ማስጠበቅ እንደሚቻል ማስተማር ያስፈልጋል።

## የአካል ቅጣት የሚያስከትላቸው ጉዳቶች

1. በሕፃናት ሰውነት ላይ የዘለቄታ የአካል ጉዳት አንዳንድ ጊዜም ሞት ሊያስከትል ይችላል።
2. ሥነ ሥርዓትን ለማስጠበቅ ሲባል በጉልበት መጠቀም አመፅን ስለሚያስተምር በዚህ ሁኔታ የሚያድግ ሕፃን በልጅነቱም ሆነ ዐዋቂ ሲሆን ተደባዳቢ ሊሆን ይችላል።
3. በመሠረቱ ኃይል የሰዎችን ሰብዓዊ ክብር የሚፃረር ነው። ሕፃናት የራሳቸው ክብር ስላላቸው በኃይል መጠቀም ሰብዓዊ ክብራቸውን መድፈር ይሆናል።
4. የአካል ቅጣት በሚያደርሰው ተፅዕኖ ምክንያት የሕፃናት በራስ መተማመንና ከሌሎች ጋር ተግባብቶ የመኖር ባሕርያቸው ይቀንሳል።
5. በአካል ላይ ከሚደርሰው ጉዳት በተጨማሪ በሕፃናቱ የወደፊት ሕይወት ላይ የማይሽር የሕሊና ጠባሳ ሊያስከትል ይችላል።
6. በትምህርት ቤት ተማሪውን «ትምህርት ለምን አልገባህም?» ብሎ መደብደብ ተማሪውን ወደ ኃይልና አመጽ የሚገፋፋ ነው። ስለሆነም የአካል ቅጣት በአጠቃላይ ከጉዳቱ በቀር በሕፃናቱ ባሕርይ ላይ ተፈላጊና ገንቢ የሆነ ለውጥ አያመጣም።

## ለአካል ቅጣት ምክንያት የሚሆኑ ሁኔታዎች

በኅብረተሰብ ውስጥ ለሕፃናት በደል ምክንያት ከሚሆኑ ሁኔታዎች መካከል ድህነት፣ ሥራ አጥነት፣ የቤተሰብ መላላትና መፍረስ፣ የመጠጥና የዕፅ ሱሰኝነት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በአገራችን ሕፃናት በወላጆችና አሳዳጊዎች፣ የቤት ሠራተኞች፣ መምህራንና በሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች ይደበደባሉ:: አንዳንድ ጊዜ የሕፃናት ጥፋትና ቅጣት ተመጣጣኝ ሆኖ አይገኝም:: በአንድ ወቅት በወጣ «ፖሊስና እርምጃው» በተሰኘው ጋዜጣ አንድ ወላጅ ልጁን ለምን 10 ሣንቲም ሰረቅህ ብሎ እጆቹን አስሮ በጣቶቹ መካከል ጭድ በመነስነስ በእሳት ሲለበልብ የሕፃኑ 10 ጣቶች ከጥቅም ውጭ እንደሆኑ ተዘግቧል:: ይህ አሳዛኝ ድርጊት ከሕፃኑ ጥፋት ጋር በምንም መለኪያ ተመጣጣኝ አይደለም:: የአካል ቅጣትን አሳሳቢነት አጉልቶ ለማሳየት በአንድ ሌላ ሕፃን ላይ የደረሰ ችግር በምሳሌነት ማየት ይቻላል::

በአንድ አካባቢ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አራት ሕፃናት ከእናትና አባታቸው ጋር በአንድ ቤት ውስጥ ይኖራሉ:: እነዚህ ሕፃናት በታላቅ ወንድማቸው ሁልጊዜ ጥቃት ይደርስባቸው ነበር:: ወንድማቸው ይደበድባቸዋል ከመጠን በላይም ያሰቃያቸዋል:: ከአራቱ ሕፃናት መካከል የ6 ዓመቱ ሕፃን ከድብደባው የተነሣ ከመጠን በላይ የፍርሃት ስሜት አደረበት:: በተለይም ወንድማቸው ገና ከሩቅ ሲመጣ ካዩት ወይም ድምፁን ከሰሙት ሁሉም ይደበቃሉ:: ይህ ሁኔታ በተለይም ለልጆቹ እናት ከፍተኛ ችግር ፈጠረ:: የ6 ዓመቱ ሕፃን ሌሊት መተኛት አልቻለም:: ከእንቅልፍ እየባነነ ይጮኻል፤ መጣብኝ እያለ ይረበሻል:: ነገሩን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ ሕፃናቱና ታላቅ ወንድማቸው የሚኖሩት በአንድ ቤት ውስጥ መሆኑ ነው:: ይህ አሳዛኝ የሕፃናት አኗኗር የሚያሳየን የአካል ጥቃት /ድብደባ/ የሚጐዳው አካልን ብቻ ሳይሆን የሕፃናትን ሥነ አእምሮና ማኅበራዊ ሕይወት ጭምር መሆኑን ነው::

ሕፃናት ሰው በመሆናቸው ወላጆች መብታቸውን ማክበር ይገደዳሉ:: ይህን በማስመልከት ፒተር ኑዌል የተባሉ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ «ሕፃናት ሰዎች እንጂ የወላጆች ንብረቶች አይደሉም:: በመሆኑም ወላጆች መብቶቻቸውን መግፈፍ አይችሉም::» ብለዋል::

በአገራችን የሕፃናት አካላዊ ቅጣት ሥር የሰደደ ችግር ነው:: የሕፃናት ደህንነት ጥበቃና ጥቃት ተከላካይ ማኅበር ስለወላጆች አካላዊ ቅጣት (Family Violence Against Children) በአዲስ አበባ በአካሄደው ጥናት ከተጠየቁት ሰዎች መካከል 85 % የሚሆኑት በወላጆቻቸው ልዩ ልዩ አካላዊ ቅጣቶች እየተፈጸሙባቸው እንዳደጉ ተናግረዋል:: ይህ የችግሩን ስፋት የሚያመላክት ነው::

ሕፃናት አካላዊ ቅጣት የሚደርስባቸው ሌላው ቦታ ትምህርት ቤት ነው:: የሕፃናት ደህንነት ጥበቃ ማኅበር ስለትምህርት ቤት ዲሲፕሊንና በሕፃናት ላይ የሚፈጸም በደል (School Disicipline and child Abuse) በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች በአካሄደው ጥናት አጥኚዎች ከጠየቋቸው ተማሪዎች መካከል 40.3% የሚሆኑት በትምህርት ቤት ልዩ ልዩ አካላዊ ቅጣቶች

እንደተፈፀሙባቸው ተናግረዋል::

በትምህርት ቤት በዲሲፕሊን ስም አካላዊ ቅጣቶች በተማሪው ላይ ሲፈጸም በአብዛኛው ችግሮቹ የሚመነጩት ከተማሪው ቁጥጥር ውጭ ከሆኑ ሁኔታዎች ነው:: የዲሲፕሊን ችግር ምንጭ የሚሆኑ ሁኔታዎች ብዙ ናቸው:: እነዚህም ተማሪው ራሱ፣ መምህሩ፣ ወላጆች፣ የትምህርት ቤቱ አካባቢና የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ናቸው:: የዲሲፕሊን ችግር መነሻዎቹ ብዙ ቢሆኑም ለሁሉም ችግሮች በጥፋተኝነት የሚደበደበው ተማሪው በመሆኑ እርምጃው ከችግሩ መነሻ ጋር የተገናኘ አይደለም::

## የአካል ቅጣትና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ

የአካል ቅጣትን በሚመለከት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተደነገገውን ከመመርመራችን በፊት ሌሎች ሕጎች ምን እንደሚሉ እንመለከታለን:: አገራችን በ1984 ዓ.ም የተቀበለችው የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን በአንቀጽ 19፣24/3/ እና 37 በሕፃናት ላይ ምንም ዓይነት አካላዊ ቅጣት እንዳይፈጸምባቸው ፈራሚ አገሮች፣ የሕግ፣ የአስተዳደር፣ የማኅበራዊና የትምህርት እርምጃዎች እንዲወስዱ ይጠይቃል::

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስትም አንቀጽ 36 ሕፃናት በትምህርት ቤት ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በአካላት ላይ



ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔ ኢሰብዓዊ ቅጣት ነፃ መሆናቸውን ያረጋግጣል::

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 548/1/ አንድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ 15 ዓመት ያልሞላውን ወይም አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ሰውነት፣ አእምሮ ወይም ጤና በሚጐዳ ሁኔታ ከቀጣ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን ተደንግጓል:: ይሁን እንጂ በዚሁ ድንጋጌ በ548/2/ ላይ ሕጋዊና ልከኛ የመቅጣት መብት እንዳልተከለከለ ተመልክቷል::

### ቁጥር 548:- ልጆችን ስለመጉዳት

1. አሥራ አምስት ዓመት ያልሞላውን ልጅ ወይም አካለ መጠን ያልደረሰውን ሰው የሚጠብቅ ወይም በአሳፊነት የሚያሣድግ ሰው የልጁን ሰውነት ወይም አእምሮውን ወይም የጤናውን እርምጃ እስከ ማበላሸት ወይም በጣም የሚያሰጋ እስከ መሆን ሆነ ብሎ ከመጠን በላይ ያሠራ፣ ልጁን ችላ ያለ፣ የጐዳ ወይም የመታ ሰው፤ አስፈላጊ ሲሆን በቤተዘመድ ላይ ካለው መብቱ የሚወገድ መሆኑ ሳይቀር ካንድ ወር በማያንስ እስራት ይቀጣል::
2. ሕጋዊና ልከኛ የሆነ የመቅጣት መብት በዚህ ውሳኔ መሠረት አያስቀጣም:: /ቁጥር 64/

ይህ ድንጋጌ አንዳንድ ጥያቄዎች የሚያስነሳ ነው:: አንደኛ ሕጋዊ ቅጣት በሕግ የተፈቀደ መሆኑ ቢታወቅም ልከኛ ቅጣት ግን መለኪያ የለውም:: ይህ በሰዎች ስሜት

የሚመራ በመሆኑ አንድ ዓይነት ደረጃ ሊኖረው አይችልም:: አንድ ሰው ልጁን በሚቀጣበት ጊዜ በንዴት በመሆኑ ይህ ልከኛ ቅጣት ስላልሆነ እዚህ ላይ አቆማለሁ በማለት ድርጊቱን ለመቆጣጠር አይችልም::

የዚህ ድንጋጌ ሌላው ችግር ከሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽንና ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ጋር ያለመጣጣሙ ነው:: የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ከላይ እንደተጠቀሰው ሕፃናት ምንም ዓይነት አካላዊ ቅጣት እንዳይፈጸምባቸው ይከላከላል:: የፌዴራል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36 በተለይ በትምህርት ቤቶችና በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ሕፃናት ከአካላዊ ቅጣት ነፃ መሆናቸውን ያረጋግጣል:: የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ግን ቀላል ቅጣትን በመፍቀድ ከባድ ቅጣትን ብቻ ስለሚከለክል ከሕገ መንግሥቱና ከኮንቬንሽኑ ጋር አይጣጣምም::

የወንጀለኛ መቅጫው ሕግ በዲሲፕሊን ስም አካላዊ ቅጣት የሚፈቅደው ለወላጆችና አሳዳጊዎች ብቻ ሳይሆን ለፍርድ ቤቶችም ነው:: አንድ ወጣት አጥፊ በሌሎች ቅጣቶች ከጥፋት እንደማይመለስ ፍርድ ቤቱ ካመነና ልጁ ጤናማ መሆኑን ካረጋገጠ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 172 መሠረት በአርጩሜ ወይም በአለንጋ ከ12 ጊዜ በማይበልጥ ጀርባው ላይ እንዲገረፍ ማዘዝ ይችላል::

ይህንኑ የፍርድ ቤትን አካላዊ ቅጣት የማዘዝ ሥልጣን የሚያጠናክረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 64 «ከደንበኛው ሕሊናዊ ልምድ ወሰን ያልወጡ የጠባይ ማረም መብት ወይም የሥነ ሥርዓት ማስፈጸም ሥልጣናዊ መብት ያላቸው ተግባሮች» በሕግ የተፈቀዱና በወንጀል የማያስጠይቁ መሆናቸውን ደንግጓል::

በዲሲፕሊን ስም የአካል ቅጣት የሚፈቅደው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ብቻ ሳይሆን የፍትሐብሔር ሕግም ነው:: በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 267 /2/ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ትምህርቱን በሚገባ እንዲማር ለማድረግ ቀላል የአካል ቅጣት መፈጸም እንደሚችሉ ተመልክቷል:: አሁንም ቀላል ቅጣት መመዘኛ የሌለው ስሜታዊ ግምት በመሆኑ እንደ ወንጀለኛ መቅጫው ድንጋጌ የአፈጻጸም ችግር አለው::

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት የወንጀለኛ መቅጫ ድንጋጌዎች ከሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽንና ከፌዴራል ሕገ መንግሥት ጋር አይጣጣሙም:: ሕገ መንግሥት የሕጐች ሁሉ የበላይ ስለሆነ ከእርሱ ጋር የማይጣጣሙት ሕጐች ሁሉ ተቀባይነትንና ተፈጻሚነት የላቸውም:: በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች እስከ አሁን በግልፅ ባይሻሩም እንደተሻሩ ይቆጠራል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ድንጋጌዎች ተሻሽለው ከሕገ መንግሥቱና ከሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ጋር እንዲጣጣሙ ለማድረግ የግድ የወንጀለኛ መቅጫው ሊስተካከል ይገባል::

## ስወሳጆች

ቤተሰብ የኅብረተሰብ መነሻ መሠረት ነው:: የቤተሰብ ዋነኛ ተጠሪዎችና የልጆች የመጀመሪያዎቹ መምህራን አባትና እናት ናቸው:: በተለይ እናት ዘጠኝ ወር አርግዛ፣ ደምና እስትንፋሷን አጋርታ ከመውለድ ጀምሮ ጡቷን አጥብታ እስከማሳደግ ድረስ ከማንኛውም የቤተሰብ አባል የቀረበ ግንኙነት ስላላት ልጆችን በማስተማርም ሆነ በመንከባከብ ረገድ ቀዳሚውን ሥፍራ ትይዛለች::

ቀጣዩን የኃላፊነት ደረጃ የሚይዘው ደግሞ አባት ነው:: ሕፃኑ አካባቢውን ለመገንዘብና ራሱን ከአካባቢው ጋር ለማስማማት የሚጥረው በቅድሚያ የእናቱንና የአባቱን ቀጥሎም የወንድሙንና የእኅቱን ብሎም የቅርብ ቤተሰቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በመመልከትና በመከተል ነው:: እናትና አባት የሕፃኑን ቀዳሚ የዜግነት ሥርዓተ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ጀምሮ ልጅን በማስተማር ረገድ የሚጫወቱት ግንባር ቀደም ሚና ጆሴፍ ሚዛን የተባሉ የትምህርት ባለሙያ "A Child Comes to the First Lesson of Citizenship on Mother's Knee and Father's Kiss." በማለት ይገልጹታል:: በእርግጥ አንድ ሕፃን በእናቱ ጭን ላይ ተቀምጦ ከንጿን ተንተርሶና ጡቷን ጉርሶ ቀና ብሎ ፊቷን እየተመለከተ ከፈገግታዋ ደስታን፣ ከመከፋቷ ሀዘንን፣ ከንዴቷ ቁጣን የሚገነዘበው፤ ባለፈና በአገደመ ቁጥር ሊስመው ጉንበስ የሚል አባቱን ፊት እየዳበሰ ነው:: «ከመሠረታዊዎቹ የትምህርት ኤጀንሲዎች መካከል



አንዱና ዋነኛው ቤተሰብ ነው::» የተሰኘውም ብሂል መነሻውም ይኸው እውነታ ነው::

በተጨባጭ እንደሚታየው ሕፃናት አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት በአካባቢያቸው ነው:: በቤተሰብና በልጆች መካከል ያለው ግንኙነትም ትምህርታዊ ነው::

የልጆች ሥነ-ዕድገት ሊቃውንት እንደሚያረጋግጡት ደግሞ በሰው የሰብዕና ልማት የመጀመሪያዎቹ አምስት የሕፃንነት ዓመታት በልጁ ዘላቂ ሕይወት ውስጥ እጅግ ወሳኝ የባሕርይ መሠረት የሚጣልባቸው ጊዜያት (Formative Periods) ናቸው:: ልጆች በዚህ ዕድሜ ክልል የሚሠሩት ጥሩም ሆነ መጥፎ ግንዛቤ በቀጣይ ሕይወታቸው ላይ ብርቱ ተፅዕኖ ሊያስከትል እንደሚችል ጥናቶች ያመለክታሉ::

በዚህ ጉዳይ ላይ ጥልቅ ምርምር ከአካሄዱት የትምህርት ጠበብት መካከል አንዱ (N.S Lovegrove) በበኩላቸው በእነዚህ የመጀመሪያ አምስት ዓመታት ውስጥ ለልጆች ቋንቋና ሥነ ሥርዓትን ወግንና ልማድን እንደዚሁም በጐ ዝንባሌዎችንና ሃሳቦችን የሚያሳውቁት ቀዳሚ መምህራን እናትና አባት መሆናቸውን ገልጸው ቤት ቀዳሚው ት/ቤት ወላጅም ቀዳሚው መምህር መሆኑን አስገንዝበዋል::

አንድ የትምህርት ባለሙያ:- አንድ ብልህ አባት ከአያሌ የት/ቤት ሥራ መሪዎች ይበልጥ ልጅን

የማስተማር ሚና እንደሚጫወትና የልጅ የመጀመሪያው ትምህርት ማቅለሚያ መጽሐፍም የእናቱ ፊት እንደሆነና ሰው በቤቱ አምሳል እንደሚቀረጽ አስመልክተው ሲጽፉ:- "A wise father is more than hundred school masters. The mother's face is the child's first lesson book. Home makes the man" ብሏል::

ይህ የወላጆች ግንባር ቀደም የማስተማር ሚና ልጁ ወደ መደበኛ ት/ቤት ከገባም በኋላ ይቀጥላል:: የልጁን መሠረታዊ ፍላጎቶችና የትምህርት መገልገያ መሣሪያዎች በማሟላት በሚያደርጉት እንክብካቤ አለኝታነታቸውን በማረጋገጥ ከመምህራንና ከት/ቤት ማኅበረሰብ ጋር የቀረበ ግንኙነት በመፍጠር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ተከታትሎ በመፍታት... ወዘተ በትምህርቱ የተሻለ ተሳትፎ እንዲያደርግና የላቀ ውጤት እንዲጨብጥ ያግዙታል::

የልጆች ቀዳሚ መምህራን የሆኑት ወላጆችና በቀለም አባትነት የሚታወቁት የት/ቤት መምህራን ግንኙነት ልጆችን አሰልጥኖ ለብቁ ዜግነት የማብቃቱ ሂደት ፍሬያማነት የሚረጋገጥበት መሆኑን በማስመልከት ኤስ ቢ ክሪሽና / S.B. Krishina / ሲጽፉም:- "Close Co-Peration between the parent who is the first teacher and the teacher who is the second parent is the very foundation on which rests the fruitfulness of the training imparted in our institution." ብሏል::

በእርግጥም በወላጆችና በት/ቤት መካከል ጠንካራ



ግንኙነት ከተፈጠረ እንደ ኤል.ኢ. ዋስተን (L.E.Wastrn) እምነት ወላጆች:-

- የትምህርትን እንቅስቃሴ በቅርበት ለማወቅ ስለሚችሉ መምህራንን ያግዛሉ::
- የማስተማርን ሥራ ውስብስብነት በመረዳት መምህራንን ያከብራሉ::
- ዘመናዊ የልጅ አያያዝና አስተዳደግ ዘዴን ከመምህራን በመረዳት በየቤታቸው ተግባራዊ ያደርጋሉ:: ከልጆቻቸው ጋር የተሻለ ግንኙነት ይፈጥራሉ::
- ለት/ቤቱ ደንብና ሥርዓት አከባበር የበኩላቸውን ትሳትፎ ስለሚያደርጉ ለአሉባልታ ጆሮ አይሰጡም::
- ስለልጆቻቸው ዝርዝር ሁኔታ ለመምህራን በመንገርና በማሳወቅ ለሕፃኑ ተገቢው እገዛ እንዲደረግለት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ::
- በተለያዩ ዕውቀትና ሙያቸው እንደዚሁም በገንዘብና ጉልበታቸው የት/ቤትን እንቅስቃሴ ያግዛሉ::
- የልጆቻቸውን የትምህርት ቤት ውሎ በመከታተልና በመገንዘብ ተገቢውን እገዛ ያደርጉላቸዋል::
- ልጆቻቸውም የወላጆቻቸውንና የመምህራኑን መቀራረብ በማየት በራስ የመተማመንና የደህንነት ስሜትን ይላበሳሉ::
- መምህራን ልጆችን ከማራቅ ይልቅ በማቅረብ

በመቅጣት ፈንታም ፍቅርን በማሳየት የመንከባከብን ፋይዳ ለወላጆች ለማስረዳት ዕድል ያገኛሉ::

* ወላጆችም ት/ቤትን እንደ ሁለተኛ መሥሪያ ቤታቸው በመቁጠር አዘውትረው ለመምጣት ይገፋፋሉ:: *«ለት/ቤቱ ምን ጠቃሚ ነገር ልሥራ?»* የሚል ስሜት ያድርባቸዋል::

በአጠቃላይ የት/ቤቱ አጋር ሆነው በመሥራት የተሻለ ውጤት እንዲገኝ ይጥራሉ:: ይህ ዓይነት የቀረበና የጠነከረ ግንኙነት ለወላጆችም ሆነ ለመምህራን በተለይም ለተማሪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጥ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ያስገነዝባሉ:: በእርስዎ ት/ቤትስ ይህን ጠንካራ ግንኙነት ፈጥረዋል? ካልፈጠሩ ይፍጠሩ! ከፈጠሩ ያጠናክሩ!



## ዋቢ መጻሕፍት


1. <u>መጽሐፍ ቅዱስ</u>፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ለኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታተመ፣ 1980 ዓ.ም፣ ናይሮቢ
2. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት</u>፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1972 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ
3. <u>ሥነ ምግባርና የሕፃናት አስተዳደግ መሠረተ-ሃሳቦች</u>፣ ሽመልስ አሰፋ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1994 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ
4. <u>ዕቀበተ ሕፃናት</u>፣ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የሕፃናትና ቤተሰብ ጉዳይ መምሪያ፣ 1988 ዓ.ም ፣አዲስ አበባ
5. <u>ሕፃናትን ለመረዳትና ለመርዳት አስፈላጊ ስልቶች</u>፣ ጥሩ ሰው ተፈራ /ዶ/ር/፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ
6. <u>ልጆችን ወደ እውነት መምራት</u>፣ ዓለማየሁ ማሞ፣ 1993 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ
7. <u>የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ንባቡ ከነትርጓሜው</u>፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ
8. <u>አርባእቱ ወንጌል ንባቡና ትርጓሜው</u>፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

9. በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ በደሎችና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ /ያልታተመ/፣ አያሌው ወ/ሰማዕት /ከሕፃናት ደህንነት ጥበቃ ማኅበር/፣ 1992 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

10. የሕፃናት ባሕርያትና የንባብ ልምድ /ያልታተመ/፣ ቡልቲ ጉተማ /ዶ/ር/፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት ለአዘጋጀው ፓናል የቀረበ፣ 1991፣ አዲስ አበባ

11. የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን /ጥናታዊ ጽሑፍ/፣ ሽመልስ አዱኛ፣ 1989 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

12. የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን፣ የሕፃናት፣ ወጣቶችና ቤተሰብ ደኅንነት ድርጅት፣ ኢሜጅ ማተሚያ ቤት፣ 1984፣ አዲስ አበባ

13. ትዳርና የቤተሰብ ሕይወት ክፍል 1 እና 2፣ ተሾመ ነጋሽ፣ 1992 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

14. የፍቅር ምሥጢር፣ ዲ/ን መልአኩ አስማማው፣ 1993 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

15. Child Development, Burk, Alimond Beckon, Advision of Simon and Shuster Inc, 2nd Edition, 1991, USA.

16. Childhood and Adolescence, Church Josph, and Stone, L.Josph, Randonm house 1nc, 2nd Edition, New York.

17. Comparative Survey of Institutionalized and Natural Home Children with Respect to Adjustment



and Intellectual Development, Addis Ababa University, 1982, Addis Ababa.

18. St. John Magazine, St. John Coptic Orthodox Church, Vol. 13 No. 135, April 2001, USA.

19. St. John Magazine, St. John Coptic Orthodox Church, Vol. 14 No. 145, February 2002, USA.

20. St. John Magazine, St. John Coptic Orthodox Church, Vol. 13 No. 142, November 2001, USA.

21. The States of the world's Children 2002, United Nations Children's fund (UNICEF), USA.

22. UNICEF Annual Report /2001/, United Nations Children Fund /UNICEF/. USA.

23. Children's Voice, The News Letter of ANPPCA – Ethiopia Chapters, Volume 3 No. 2, December 1997, Addis Ababa.

24. Children's Voice, The News Letter of ANPPCAN-Ethiopia Chapter, Vol. 2. No. 2, December 1996, Addis Ababa.

25. Children's Voice, The News Letter of ANPPCAN-Ethiopia Chapter, Vol. 7. No. 1, June 2001, Addis Ababa.

26. Children's Voice, The News Letter of ANPPCAN-Ethiopia Chapter, Vol. 6. No. 2, June 2000, Addis

Ababa.

27. Children's Voice, The News Letter of ANPPCAN-Ethiopia Chapter, Vol. 5. No. 1, June 1999, Addis Ababa.

28. Childhood and Adolescence, Church Josph, and Stone, L. Josph, Randonm house Inc, 2nd edition New York.

29. Developmental Psychology, Harlock Elizabet B., Ta-Ta OM c. Graw Hill Publishing Co. Put Newdelhi, 5th edition, 1980.

30. Dibs in Search of Self, Virginia M. Axline, 1964, USA

31. How to relate to Children, His Holiness Pope Shenouda, 1994, Cairo, Egypt.

32. Introduction to Psychology, Morgan T. Cliferd, M.C Growhill book Co. 1ne, 3rd edition, 1966, USA

33. What is Man? H.H. Pope Shenouda III, 1997, Cairo

34. Salvation In the Orthodox concept, H.H. Pope Shenouda III, 1999, Cairo.



ይህ መጽሐፍ ተወዳጅ የሆነ የሕፃናት ሞግዚት ነው፡፡ ወላጆች (አሳዳጊዎች) ይህን መጽሐፍ አንብበው፣ ሕፃናት አካላዊ፣ አእምሮአዊና መንፈሳዊ ብቃት እንዲኖራቸው ለመርዳት ያስችላቸዋል፡፡

ከስጦታዎች ሁሉ ሕፃናትን የሚያስደስት ስጦታ ፍቅር ነው፡፡ ስለዚህ ሕፃናትን በፍቅር ለማሳደግ የፍቅርን ትርጉም በውል ለመረዳት ይህን መጽሐፍ ማንበብ ይጠቅማል፡፡ በወጣት ደራሲ ለወጣቶች የተሰጠ የመጀመሪያ ገጸ በረከት፡፡

ቀሲስ ከፍያለው መራሒ
(ማስተር ኦፍ ዲቪኒቲ)

አከፋፋይ ፡- ዋሸራ መጻሕፍት መደብር
ክፍለ ሀገር አውቶቢስ ተራ
አዲስ ከተማ ት/ቤት ፊት ለፊት
ስልክ ቁጥር 768940

ዋጋው ብር 10.00